የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.31
ADDIS ABABA 17th, March, 2025

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፸/፪ሺ፲፯
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ …………………………………………ገጽ ፲፯ሺ፱፻፵፭

## Content

Regulation No. 570/2025
Council of Ministers Value Added Tax Regulation ……………………………………..Page 17945

## ደንብ ቁጥር ፭፻፸/፪ሺ፲፯

## የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፩/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፸፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር ፭፻፸/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ **“ኮሚሽን”** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ (እንደተሻሻለ) የተቋቋመው የጉምሩክ ኮሚሽን ነው፤

## REGULATION No. 570/2025

## VALUE ADDED TAX REGULATION

These regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 72 Sub-Article (1) of the Value Added Tax Proclamation No. 1341/2024.

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

These Regulations may be cited as the “Council of Ministers Value Added Tax Regulation No 570/2025”.

**2. Definitions**

In these Regulations, unless the context requires otherwise፤

1/ “**Commission**” means the Customs Commission established under the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021;

፪/ **"ሚኒስቴር"** ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፤

፫/ "**አዋጅ**" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፩/፪ሺ፲፯ ነው፤

፬/ **"የታክስ አስተዳደር አዋጅ"** ማለት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺ፰" ነው፤

፭/ **"የታክስ ባለስልጣን"** ማለት እንደሁኔታው የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሰረት የውክልና ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ ነው፤

፮/ **"የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር"** ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ክፍል ሦስት ምዕራፍ ሁለት መሰረት የሚሰጥ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ነው፤

፯/ **"የተጨማሪ እሴት ታክስ"** ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፩/፪ሺ፲፯ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፤

፰/ በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላት እና ሐረጎች የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር እንደአግባብነቱ በአዋጁ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

## ክፍል ሁለት
## ታክስ የመሰብሰብ ሥልጣን እና ምዝገባ

### ፫. ታክስ የመሰብሰብ ሥልጣን

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሰረት ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ ውክልና ሊሰጥ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡

ሀ) የገቢዎች ሚኒስቴር በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር ውስጥ ቢሮ የሌለው ከሆነ፤ ወይም

2/ "**Ministry**" means the Ministry of Finance;

3/ "**Proclamatio**n" means the Value Added Tax Proclamation No. 1341/2024;

4/ "**Tax Administration Proclamation**" means the Tax Administration Proclamation No. 983/2016;

5/ "**Tax Authority"** means, as the case may be, the Ministry of Revenue, or a Regional or City Administration Revenue Bureau with delegated authority under Article 4 of the Proclamation;

6/ "**TIN**" means a taxpayer identification number issued under Part Three Chapter Two of the Tax Administration Proclamation;

7/ "**VAT**" means the Value Added Tax imposed by the Value Added Tax Proclamation No. 1341/2024;

8/ A term used in these Regulations has the same meaning as in the Proclamation or the Tax Administration Proclamation, as the case may be, unless the context requires otherwise.

## PART TWO
## REGISTRATION AND POWER TO COLLECT TAX

### 3. Power to Collect Tax

1/ A delegation under Article 4 of the Proclamation to a Regional or City Administration Revenue Bureau may be made only if the following conditions are satisfied:

a) The Ministry of Revenue has no office in the Region or City Administration; or

ለ) በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር የኢንተርኔት ግንኙነት ውስን በመሆኑ ወይም ጭራሹንም የሌለ በመሆኑ ምክንያት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ታክስ ለማስታወቅ እና ለመክፈል የማይችሉ ሆኖ ከተገኘ::

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፬ መሠረት የሚሰጠው ውክልና የሚያገለግለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመሰብሰብ ሲሆን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስን መወሰን፤ የግብአት ታክስን ክሬዲት ማድረግ፤ ተመላሽ መስጠት፤ በታክስ ሕጉ በተፈቀደው መሠረት አቅርቦቶች ታክስ የሚከፈልባቸው፣ ከታክሱ ነጻ እንዲሆኑ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆን መወሰንን ጨምሮ ሌሎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተያያዘ የተሰጡ ኃላፊነቶች በሙሉ የገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናሉ::

፫/ ታክሱን ለመሰብሰብ ውክልና የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ በውክልናው መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሰበሰበውን ታክስ ወሩ በተጠናቀቀ በአምስት ቀን ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ማድረግ አለበት።

፬/ የገቢዎች ሚኒስቴር ከግለሰብ ግብር ከፋዮች ከተሰበሰበው ታክስ ውስጥ የየክልሉ ድርሻ የሆነውን ታክሱ ገቢ የሆነበት ወር በተጠናቀቀ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ የገቢው ባለቤት ለሆነው ክልል ማስተላለፍ አለበት፡፡

፭/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር ረገድ ሊያከናውኑት የሚገባ ተግባር በ ፌደራል እና በክልል የገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች በሚፈረም የጋራ መግባቢያ ስምምነት ይወሰናል፡፡

b) VAT registered persons in the Region or City have no or limited capacity to file and pay tax electronically due to no or limited internet connectivity in the region or city.

2/ A delegation made under Article 4 of the Proclamation shall be limited to the collection of the VAT, with all other aspects of the VAT will remain to be the sole responsibility of the Ministry of Revenue, including VAT assessments, the crediting of input tax, refunds, and the determination of supplies as taxable, exempt, or zero-rated.

3/ A Regional or City Administration Revenue Bureau collecting VAT pursuant to a delegation shall transfer the entire amount of the VAT collected to the Ministry of Revenues within five days after the end of each month.

4/ The Ministry of Revenue must transfer the region's share of the revenue collected from individual taxpayers to the respective regional government within five days after the end of the month in which the revenue was transferred.

5/ Subject to the provisions of sub article (2) of this article, the specific tasks to be undertaken by regional revenue collection offices in relation to value-added tax administration shall be determined through a mutual agreement between the federal and regional revenue collection offices.

፬/ **<u>የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት</u>**

ለተመዘገበ ሰው በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት የሚሰጠው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን የሚጨምር መረጃ ሊይዝ ይገባል፡-

፩/ የተመዘገበውን ሰው ስም፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

፪/ ለተመዘገበው ሰው የሚሰጠውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር፣

፫/ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበትን ቀን፣ እና

፬/ ምዝገባው የጸና የሚሆንበትን ቀን።

፭/ **<u>ምዝገባን ስለማገድ</u>**

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፰) አፈጻጸም የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባው የታገደበት ሰው፣ ምዝገባው በታገደበት ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን መፈጸም የለበትም:-

ሀ) ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት መፈጸም፣

ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት እና የዴቢት ሰነድ መቁረጥ፣

ሐ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲሰጠው ወይም የግብአት ታክስ ተመላሽ እንዲፈቀድለት መጠየቅ፣ ወይም

መ) ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በሚያከናውንበት በማናቸውም ሰነድ፣ እና ማናቸውም ድረ-ገጽ፣ የማሕበራዊ ሚዲያ አድራሻ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግብይት በሚያከናውንበት መድረክ የተመዘገበ ሰው መሆኑን መግለጽ፡፡

4. **<u>VAT Registration Certificate</u>**

A VAT registration certificate issued to a registered person under Article 14 Sub-Article (5) of the Proclamation shall include the following details:

1/ The name, address, and TIN of the registered person;

2/ The unique VAT registration number of the person;

3/ The date that the certificate was issued; and

4/ The date from which the registration takes effect.

5. **<u>Suspension of Registration</u>**

1/ For the purposes of Article 16 Sub-Article (8) of the Proclamation, a person whose VAT registration has been suspended shall not, during the period of the suspension:

a) make any taxable supplies;

b) issue any tax invoices, or credit or debit notes;

c) apply for a VAT refund or claim an input tax credit; or

d) Hold out that the person is a registered person, including on any documentation used by the person, and on any website, social media account, or other electronic platform through which the person carries on their taxable activity.

፪/ ምዝገባው የታገደበት ሰው የምዝገባው መታገድ በፀናበት ቀን በአዋጁ አንቀጽ ፵፰ መሠረት ወደፊት የተሸጋገረ ክሬዲት ሊደረግ የሚችል ሂሳብ ያለው እንደሆነ ክሬዲት ሊደረግ የሚገባው ሂሳብ እገዳው እስከሚሻር ድረስ እንዲቆይ ሆኖ እገዳው ሲነሳ ተፈፃሚ ይሆናል።

፫/ ምዝገባው የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማከናወኑን በቋሚነት የማይቀጥል ከሆነ ምዝገባው ታግዶ ባለበት በማናቸውም ጊዜ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።

፬/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች አቅርቦት ለመቀጠል ከፈለገ ቢያንስ ከአስራ አምስት (፲፭) ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምዝገባ የታገደበት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት እገዳው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ ካላቀረበ የእገዳው ጊዜ እንደተጠናቀቀ ምዝገባው ይሰረዛል።

## ፮/ ምዝገባን ስለመሰረዝ

፩/ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው ምዝገባው ከጸናበት ቀን አንስቶ ለተከታታይ ስድስት (፮) ወር ምንም አይነት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያለማከናወኑን ካረጋገጠ ምዝገባው ከፀናበት ቀን አንስቶ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል። ሆኖም የታክስ ከፋዩ ምዝገባ መሠረዝ ግዴታውን ባለመወጣቱ በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የሚጣልበትን መቀጫ የሚያስቀር አይሆንም፡፡

2/ If a person whose VAT registration has been suspended has an uncredited amount of excess input tax credit carried forward under Article 48 of the Proclamation as at the date the suspension comes into effect, the carry forward period for the excess credit shall be suspended and shall recommence once the suspension ceases.

3/ A person whose registration has been suspended shall, at any time during the period of suspension, apply for cancellation of the person's registration if the person permanently ceases to make taxable supplies.

4/ A person whose VAT registration has been suspended shall notify the Tax Authority, in writing, at least fifteen (15) days prior to again making taxable supplies.

5/ Subject to Sub-Article (3), if a person whose registration has been suspended fails to notify the Tax Authority under Sub-Article (4) of this Article during the suspension period, the person's registration shall be cancelled at the end of the suspension period.

## 6. Cancellation of Registration

1/ The tax authority may decide to cancel a taxpayer's registration if the registered individual or entity has not conducted any taxable transactions for six (6) consecutive months from the date of registration. However, this cancellation does not exempt the taxpayer from any penalties imposed under the tax administration proclamation for failure to fulfil his duties.

፪/ የታክስ ከፋዩ ምዝገባ ከተሰረዘ በኋላ ያላስታወቀውና ያልከፈለው የታክስ ዕዳ መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ከነመቀጫው ለመጠየቅ ይችላል፡፡

፯/ **የቅርንጫፍ ምዝገባ**

፩/ ይህ አንቀጽ የአዋጁን አንቀጽ ፷፯ ለማስፈጸም አላማ የሚውል ነው።

፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የአንድ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የተለየ ምዝገባ “የቅርንጫፍ ምዝገባ” ይባላል።

፫/ የተመዘገበ ሰው አንድ ምዝገባ ብቻ ያለው መሆኑ ግዴታውን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድርበት ከሆነ የቅርንጫፍ ምዝገባ እንዲፈቀድለት ሊያመለክት ይችላል። የታክሱ ባለስልጣን ታክስ ከፋዩ አንድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ በትክክል ችግር የሚያስከትልበት መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ ይወስናል።

፬/ የተመዘገበው ሰው የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም የተለየ የቅርንጫፍ ምዝገባ ለሚያስፈልገው ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም አንድ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የቅርንጫፍ ምዝገባ እንዲፈቀድለት ማመልከት አለበት። አዲስ የሚመዘገብ ሰው የምዝገባ ማመልከቻ እና የቅርንጫፍ ምዝገባ ማመልከቻ በአንድ ጊዜ ሊያቀርብ ይችላል።

፭/ የቅርንጫፍ ምዝገባ ሊፈጸም የሚችለው የታክሱ ባለስልጣን ሲፈቅድ ብቻ ሲሆን፣ አመልካቹ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፦

ሀ) አመልካቹ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሊሆን የሚገባ ሲሆን፣ የመንግስት ተቋማትን ሳይጨምር በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ መሰረት በፈቃደኝነት የተመዘገበ መሆን የለበትም፣

2/ If a taxpayer's registration is cancelled, the tax authority retains the right to demand any unpaid taxes within the time provided under the Tax Administration Proclamation, should it be confirmed that the taxpayer has undeclared and unpaid tax liabilities.

7. **Divisional Registration**

1/ This Article applies for the purposes of implementing Article 67 of the Proclamation.

2/ For the purpose of this Article, the separate registration of a branch, division, or taxable activity is referred to as “divisional registration”.

3/ A registered person may apply for divisional registration if a single registration requiring a single VAT return imposes an onerous compliance burden on the registered person. The Tax Authority, in its sole discretion, shall decide if the applicant will experience real difficulties in filing a single VAT return.

4/ A registered person shall file a separate application for divisional registration, in the approved form, for each branch, division, or separate taxable activity for which divisional registration is sought. A newly registering person shall submit an application for registration and an application for divisional registration at the same time.

5/ Divisional registration is at the discretion of the Tax Authority and, to be eligible, the applicant must satisfy all of the following conditions:

a) the applicant must be a registered person for VAT purposes, but not a person who voluntarily applied for registration under Article 13 of the Proclamation;

ለ) ማመልከቻው የአመልካቹን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጥር የያዘ እና በአመልካቹ የተፈረመ መሆን አለበት፤

ሐ) አመልካቹ ለንግድ ስራው ሁሉ አንድ የታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ ቢደረግ፣ ይህንን ግዴታውን መወጣት ሊያደርስበት የሚችለውን ጫና ማስረዳት አለበት፤ በተለይም በማመልከቻው መሰረት ባይፈቀድለት ሊያጋጥመው የሚችለውን ችግር እና በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ለሁሉም የንግድ ስራው የተጠቃለለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ሊያቀርብ የማይችልበትን ምክንያት ማብራራት አለበት፤

መ) የቅርንጫፍ ምዝገባ የተጠየቀለት ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ገንዘብ መቀበል፣ መክፈል እና የሂሳብ መግለጫ ማቅረብን ጨምሮ ከተመዘገበው ሰው ዋና መስሪያ ቤት እና ከሌሎች የስራ ክፍሎች የተለየ ራሱን የቻለ የሂሳብ ስርአት ያለው መሆን አለበት፤

ሠ) አመልካቹ ሂሳቡን ከማጠቃለሉ በፊት የተለየ ሂሳብ ሲያዘጋጅ የነበረ መሆን አለበት፤

ረ) እያንዳንዱ የቅርንጫፍ ምዝገባ የተጠየቀለት ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ ወይም በሚገኝበት አድራሻ ተለይቶ የሚታወቅ መሆን አለበት፤

ሰ) እያንዳንዱ የቅርንጫፍ ምዝገባ የተጠየቀለት ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ከዋናው መስሪያ ቤት ጋር አንድ አይነት የሂሳብ ጊዜ እና የሂሳብ ጊዜ መጨረሻ የሚከተል መሆን አለበት፣ እና

b) the application must be in writing and include the applicant's TIN and VAT registration number;

c) the applicant must demonstrate that he will experience an onerous compliance burden if he is obliged to file a single VAT return for its entire business operations. In particular, the applicant must describe in detail the problems likely to be encountered if the application is not approved, and the reasons why a consolidated VAT return for the entire business for each accounting period cannot be filed by the due date for each period;

d) the branch, division, or separate taxable activity for which divisional registration is requested must maintain an independent accounting system, particularly, receipts and payments, and produce financial statements separate from its head office and other parts of the entity that is the registered person;

e) the applicant must already be preparing separate accounts before consolidating them;

f) the branch, division, or taxable activity for which divisional registration is requested must be separately identified by reference to the nature of its activities or its location;

g) each branch, division, or separate taxable activity must use the same accounting period and the same year-end date as the entity; and

ሸ) አዲስ የሚመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ሊያሟሉ የሚገባውን ቅደመ ሁኔታ ጨምሮ የታክሱ ባለስልጣን የሚወስናቸው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች፣

፯/ እያንዳንዱ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ተለይቶ የሚታወቅበት የቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የአመልካቹ የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለተመዘገበው ቅርንጫፍ የሚሰጠው "ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር"፣ የተመዘገበው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሲሆን፣ በቅርንጫፍ፣ በስራ ክፍል ወይም በተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውል ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መሆኑን ለማሳየት ተጨማሪ መለያ ሊኖረው ይገባል፡፡

፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፯ (፪) በተደነገገው መሰረት በታክስ ባለስልጣኑ ተለይቶ የተመዘገበ እያንዳንዱ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ራሱን የቻለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት። እያንዳንዱ ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የአመልካቹ አካል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ በተመዘገበ ሰው ላይ የተጣሉ ግዴታዎች ሁሉ ተፈጻሚ ይሆኑበታል።

፰/ የታክሱ ባለስልጣን በአዋጁ መሰረት ለቅርንጫፍ፣ ለስራ ክፍል ወይም ለተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ሊከፈል የሚገባውን ተመላሽ በአዋጁ መሰረት በተመዘገበው ሰው ወይም በተመዘገበው ሰው ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ወለድ እና መቀጫ ለማሟላት ሊጠቀምበት ይችላል።

h) such other conditions that the Tax Authority may impose, including additional conditions for a newly registering entity.

6/ Each separately registered branch, division, or taxable activity of an entity shall be issued with a TIN, VAT registration number, and VAT registration certificate that identifies it as a branch, division, or separate taxable activity of the company. The TIN, referred to as a "sub-TIN", issued to a registered branch, division, or taxable activity of a registered person shall be the TIN of the registered person with an additional identifier indicating that the TIN is a sub-TIN for use by a registered branch, division, or taxable activity of the registered person.

7/ A branch, division, or separate taxable activity of a registered person separately registered by the Tax Authority under Article 67(2) of the Proclamation shall file a separate VAT return for each accounting period. Each separately registered branch, division, or taxable activity of an entity shall be subject to all the obligations imposed on a registered person under the Proclamation and these Regulations provided that it remains to be part of the applicant.

8/ The Tax Authority may apply a refund payable under the Proclamation to a separately registered branch, division, or taxable activity of a registered person to satisfy any VAT, interest, or penalty liability of the registered person or by another separately registered branch, division, or separate taxable activity of the registered person.

፱/ ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ለዋናው መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ ተለይቶ ለተመዘገበ ቅርንጫፍ የሚያቀርበው አቅርቦት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተፈጸመ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። አቅራቢው በአዋጁ በተደነገገው መሰረት ለአቅርቦቱ የታክስ ደረሰኝ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ በአዋጁ የተፈቀደ እስከሆነ ድረስ ተቀባዩ በአቅርቦቱ ላይ ለከፈለው ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊጠይቅ ይችላል።

፲/ የተመዘገበው ሰው ዋና መስሪያ ቤት ተለይቶ ለተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል፣ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የደለደለው የጠቅላላ አገልግሎት ወጪ ዋናው መስሪያ ቤት በክፍያ ለቅርንጫፍ፣ ለስራ ክፍል ወይም ለተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የፈጸመው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል።

፲፩/ በተመዘገበው ዋና መስሪያ ቤት እና ተለይቶ በተመዘገበ ቅርንጫፍ ወይም ተለይተው በተመዘገቡ የተመዘገበው ሰው ቅርንጫፎች መካከል የሚደረግ ግብይት ተለየተው በመመዝገባቸው ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ ፸ የተመለከተው የተለየ የታክስ ጥቅም የሚገኝበት እንዳይሆን በታክሱ ባለሥልጣን ጥብቅ ክትትል ሊደረግበት ይገባል።

፲፪/ እያንዳንዱ ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል፣ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ፣ ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ተለይቶ የተሰጠውን ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጥር በመጠቀም ደረሰኝ መስጠት አለበት።

9/ A supply made by a separately registered branch, division, or taxable activity of a registered person to the head office or other separately registered part of the entity shall be treated as a supply made between related persons. The supplier must issue a tax invoice for those supplies in accordance with the Proclamation, and the recipient can claim input tax credits in respect of input tax payable in respect of those supplies to the extent allowed under the Proclamation.

10/ Expenses allocated by the head office of a registered person to a separately registered branch, division, or taxable activity of the person may be treated as consideration for taxable supplies made by the head office to the separately registered branch, division, or taxable activity.

11/ Transactions between the head office of a registered person and a separately registered part of the registered person or between separately registered parts of a registered person may be closely scrutinised by the Tax Authority to prevent the use of separate registration to obtain a tax benefit referred to in Article 70 of the Proclamation.

12/ Each separately registered branch, division, or taxable activity shall issue tax invoices using its unique sub-TIN and VAT registration number for a taxable transaction it carry out.

፲፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ለተጠቀሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታን ለሚያስከትለው የግብይት መጠን አፈፃፀም እያንዳንዱ ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፤ የስራ ክፍል፤ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ግብይት የተመዘገበው ሰው አቅርቦት ውስጥ ይደመራል፡፡

፲፬/ የታክሱ ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚደረገው የግብአት ታክስ ተቀናሽ በቅርንጫፍ ደረጃ ሳይሆን በተመዘገበው ሰው ዋና መስሪያ ቤት ደረጃ እንዲፈጸም ሊያዝ ይችላል።

፲፭/ የተመዘገበ ሰው ዋና መስሪያ ቤት ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል፣ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ምዝገባ እንዲሰረዝ ለታክሱ ባለስልጣን በጽሑፍ ሊያመለክት ይችላል። ምዝገባው የሚሰረዘው የሚከተሉት ሲሟሉ ይሆናል፦

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን ከዚህ ያነሰ ጊዜ ካልፈቀደ በስተቀር፣ የቅርንጫፍ የተለየ ምዝገባ ቢያንስ ለሁለት ዓመት ፀንቶ መቆየት አለበት፡

ለ) ማናቸውም ድርጅት ወይም ቅርንጫፍ ለቅርንጫፍ ምዝገባ የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላቱን ያቋረጠ እንደሆነ ኩባንያው ከቅድመ-ሁኔታዎች አንዱ መሟላቱ በተቋረጠ በ፴ ቀናት ውስጥ ይህንን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

ሐ) የታክሱ ባለሥልጣን ለቅርንጫፍ ምዝገባ የተቀመጡት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው የተቋረጠ ወይም ለመንግሥት ገቢ ደህንነት አስፈላጊ መስሎ ከታየው የቅርንጫፍ ምዝገባን ለመሰረዝ ይችላል።

13/ For the purposes of applying the registration threshold under Article 12 of the Proclamation, the supplies of each separately registered branch, division, or taxable activity of an entity shall be included as the supplies of the registered person.

14/ The Tax Authority may require the allocation of input tax credits under Article 29 Sub-Article (2) of the Proclamation to be made on head office basis, rather than on a division-by-division basis.

15/ The head office of a registered person may apply in writing to the Tax Authority for the cancellation of the separate registration of a branch, division, or taxable activity, or the Tax Authority may initiate a cancellation of a divisional registration. The registeration shall be cancelled upon the fulfillment of the following:

a) unless the Tax Authority approves a shorter period, the separate registration of a division must remain in effect for not less than two years;

b) if an entity or division ceases to satisfy any of the conditions imposed on divisional registration, the entity shall notify the Tax Authority in writing of the change within 30 days of the date any condition failed to be met.

c) the Tax Authority may cancel a divisional registration if the conditions for divisional registration are no longer satisfied or the Tax Authority believes that cancellation is necessary for the protection of governemnt revenue.

መ) የታክሱ ባለሥልጣን የቅርንጫፍ ምዝገባ የሚቀጥል መሆን ያለመሆኑን የመወሰን ሙሉ ስልጣን አለው።

ሠ) የቅርንጫፍ ምዝገባ መሰረዝ የጸና የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን ምዝገባው መሰረዙን ለማስታወቅ በሚሰጠው ማስታወቂያ ከተገለጸው ቀን አንስቶ ይሆናል።

## ክፍል ሦስት
## አቅርቦቶች

### ፰. የአደራ ሽያጭ እና በውክልና ስልጣን ደረጃ ስለማስተላለፍ

፩/ የዕቃው ባለቤት (ሻጭ) እቃውን በአቅርቦት ወይም በተመላሽ (የአደራ ሽያጭ) ለሌላ ሰው መስጠቱ ግብይት እንደተፈጸመ አያስቆጥርም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የዕቃ አቅርቦት ግብይት ተፈፅሟል የሚባለው ባለቤቱ የእቃውን ባለቤትነት ወደ ገዢው ሲያስተላልፍ ይሆናል።

፫/ በውክልና ሥልጣን ደረጃ ዕቃ ለአንድ ሰው ሲተላለፍ ግብይት እንደተፈፀመ አይቆጠርም።

፬/ ሚኒስቴሩ ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም የሚያግዝ መመሪያ ያወጣል፡፡

### ፱. ከቦንድድ የማምረቻ ፋብሪካ መጋዘን ዕቃ ወጪ ስለማድረግ

፩/ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፰/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) በተደነገገው መሠረት ዕቃ ከቦንድድ የማምረቻ ፋብሪካ መጋዘን ወጪ ሲደረግ ወይም የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ተፈፃሚ የሚሆንበት ማንኛውም የእቃ አቅርቦት ሲፈፀም በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የእነዚህ እቃዎች አቅርቦት እንደተፈጸመ ይቆጠራል።

d) the Tax Authority shall have sole discretion to determine if the divisional registration shall be allowed to continue.

e) the cancellation of divisional registration shall be effective from the date specified by the Tax Authority in the notice of cancellation.

## PART THREE
## SUPPLIES

### 8. Consignment Sales and Transfers in Representative Capacity

1/ The provision of goods by the owner to a person (seller) on a supply or return (consignment) basis is not a supply.

2/ A supply of goods referred to in Sub-Article (1) occurs if the owner transfers ownership of the goods to the seller.

3/ The transfer of goods to a person in a representative capacity is not a supply.

4/ The Ministry shall issue a directive for the implementation of this Article.

### 9. Removal of Goods from a Bonded Manufacturing Warehouse

1/ The removal of goods from a bonded manufacturing warehouse or any supply of goods subject to an export trade duty incentive scheme under the Export Trade Duty Incentive Scheme Establishing Proclamation No. 768/2012 (as amended) shall be treated as a supply of those goods in the course or furtherance of a taxable activity in Ethiopia.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ገበያ የዋሉ ከሆነ አቅርቦቱ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ስለሆነ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልበታል። አቅርቦቱ ተፈፅሟል የሚባለው በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሰረት እቃዎቹ ለአገር ውስጥ ገበያ ሲቀርቡ ሲሆን፣ የአቅርቦቱ ዋጋ ሽያጩ በተከናወነበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ዕቃዎች ከአዋጁ ጋር በተያያዘው አባሪ መሰረት ለውጭ ገበያ የተላኩ ከሆነ አቅርቦቱ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ይደረግበታል። በዚህ አንቀጽ መሰረት አቅርቦቱ ተፈጽሟል የሚባለው እቃው ወደውጭ አገር ሲላክ ነው።

፲. **<u>የሠራተኞች አገልግሎት</u>**

፩/ ሠራተኛ በቅጥር ውል መሰረት ለአሰሪው የሚሰጠው አገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ አይቆጠርም።

፪/ አሰሪው ለሰራተኛው፡ -

ሀ) በሠራተኛው ስም ለአቅራቢ ክፍያ የሚፈፅም ከሆነ፣ ወይም

ለ) ሠራተኛው ያወጣውን ወጪ የሚተካ ከሆነ፣ እነዚህም ክፍያዎች በጥቅማ ጥቅም መልክ ለሰራተኛ የሚሰጥ ዕቃ እና አገልግሎትን ወጪ ለመሸፈን የሚውሉ ከሆነ፣ ለሰራተኛ የሚሰጥ እቃ እና አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የተፈፀመ ባለመሆኑ አሰሪው በዚህ አይነቱ ወጪ ላይ የታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ አይችልም።

፫/ አሰሪው ለሰራተኛው በቅናሽ ወይም በነፃ የሚያቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ታክስ ይከፈልበታል፡፡

2/ If the goods referred to in Sub-Article (1) of this Article are sold in the domestic market, the sale shall be a taxable supply subject to VAT at the rate specified in Article 8 Sub-Article (2) paragraph (b) of the Proclamation. The supply shall occur when the goods are supplied in the domestic market as determined under Article 21 of the Proclamation and the value of the supply shall be equal to the fair market value of the goods at that time.

3/ If the goods referred to in Sub-Article (1) of this Article are exported as determined under Schedule 1 of the Proclamation, the supply is a zero-rated supply. Under this article, the supply is considered to occur at the time of export.

**10. <u>Services of Employee</u>**

1/ The provision of services by an employee to an employer by reason of employment is not a supply.

2/ If an employer:

a) pays a supplier on behalf of the employee; or

b) reimburses an employee, For the cost of goods or services provided to an employee as a fringe benefit, the employer is not entitled to claim any portion of the cost as an input tax credit because the goods or services provided to the employee are not used in the course or furtherance of the employer's taxable activity.

3/ Goods or services provided by the employer to the employee at a discount or free of charge are subject to tax.

**፲፩. ያገለገሉ ዕቃዎች**

፩/ ካልተመዘገበ ሰው ያገለገሉ እቃዎችን የሚገዛ ያገለገሉ እቃዎች አቅራቢ ለአዋጁ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፬) አፈጻጸም የሚከተሉትን መረጃዎችን ማረጋገጥ የሚያስችሉ በቂ ሰነዶችን መያዝ አለበት፦

ሀ) ላገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ ዕቃዎቹን ያቀረበውን ሰው ስም እና አድራሻ፤

ለ) ያገለገሉት ዕቃዎች ላገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ የቀረቡበትን ቀን፤

ሐ) የቀረቡትን ዕቃዎች ዓይነት የሚገልፅ መግለጫ፤

መ) የቀረቡትን ዕቃዎች ብዛት ወይም መጠን፤ እና

ሠ) ለአቅርቦቱ የተፈፀመውን ክፍያ፤

፪/ ያገለገሉ ዕቃዎችን የሚገዛ ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ በሚዘጋጅ የክፍያ ደረሰኝ ላይ ያገለገሉ ዕቃዎችን አቅራቢ ማስፈረም አለበት፡፡

**፲፪. የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት**

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፴፬ አፈፃፀም በዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ላይ የተሠማራ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ሊኖረው የሚገባው የውጤት ታክስ ስሌት በሚከተለው ቀመር መሠረት የሚገኘውን የገንዘብ መጠን የሚጨምር ይሆናል፦

(ሀ-ለ) x ሐ

በዚህ ቀመር ውስጥ፤

"ሀ" በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የዕድል ሙከራ የተደረገበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን፤

"ለ"በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የተሰጠው ሽልማት የገንዘብ ዋጋ፤ እና

"ሐ" የታክስ ክፍልፋይ፤

**11. Second-hand Goods**

1/ For the purposes of Article 33 Sub-Article (4) of the Proclamation, a second-hand goods supplier receiving a supply of second-hand goods from an unregistered person shall maintain sufficient records to enable the following information to be ascertained:

a) the name and address of the person supplying the goods to the second-hand goods supplier;

b) the date upon which the second-hand goods were supplied to the second-hand goods supplier;

c) description of the goods supplied;

d) the quantity or volume of the goods supplied; and

e) the consideration for the supply.

2/ A second-hand goods buyer shall get the supplier of second-hand goods signature on the payment receipt prepared with the permission of the Tax Authority.

**12. Gambling Supplies**

1/ For the purposes of Article 34 of the Proclamation, the output tax of a registered person making taxable gambling supplies for an accounting period shall include an amount calculated in accordance with the following formula:

(A – B) x C

where:

"A" is the total amounts wagered in the period;

"B" is the total monetary prizes paid out in the period; and

"C" is the tax fraction.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ስሌቱ ሲከናወን የአንድ የሂሳብ ጊዜ የገንዘብ መጠን ከዜሮ በታች ከሆነ፣ በሂሳብ ጊዜው በዚህ አንቀጽ መሰረት የተመዘገበው ሰው የውጤት ታክስ ሆኖ የሚያዝ የገንዘብ መጠን አይኖርም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ውስጥ፡-

ሀ) “የዕድል ሙከራ” ማለት፡-

(i) ሎተሪ፣ ቶምቦላ ወይም ተመሳሳይ ውድድር ማከናወን፣ ወይም

(ii) አንድ ውጤት ያለው ወይም እንዲኖረው የተደረገ ውርርድ፣ ጨዋታ፣ የስፓርት ክንውን ወይም ሌላ ማናቸውም ክንውን፤

ለ) “የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት” ማለት

(i) በማናቸውም መንገድ የተገለፀ ቢሆንም የሎተሪ፣ የቶምቦላ ወይም ተመሳሳይ የዕድል ሙከራ ወይም የውርርድ ቲኬት አቅርቦት፣ ወይም

(ii) በማናቸውም መንገድ የተገለጸ ቢሆንም የዕድል ሙከራ ወይም የውርርድ ጨዋታ ውጤትን መቀበል፣ ነው።

ሐ) “ታክስ የሚከፈልበት የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት” ታክስ የሚከፈልበት የዕድል ሙከራ ጨዋታ ነው”፤

መ) “የዕድል ሙከራ የተደረገበት ጠቅላላ ገንዘብ” የተመዘገበን ሰው በሚመለከት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የተከናወነው የሚከተሉት ድምር ነው፡-

(i) የተመዘገበው ሰው ለሚያቀርባቸው የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦቶች በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የተከፈለ ገንዘብ፣ እና

2/ Where the amount calculated under Sub-Article (1) of this Article for an accounting period is a negative amount, no amount shall be included under this Article in the output tax of the registered person for that period.

3/ In this Article:

a) “gambling event” means:

(i) the conduct of a lottery, raffle, or similar undertaking; or

(ii) a race, game, sporting event, or other event that has, or is intended to have, an outcome;

b) “gambling supply” means:

(i) the supply of a ticket, however described, in a lottery, raffle, or similar undertaking; or

(ii) the acceptance of a bet or wager, however described, relating to the outcome of a gambling event;

c) “taxable gambling supply” means a gambling supply that is a taxable supply;

d) “total amounts wagered”, in relation to a registered person for an accounting period, means the sum of:

(i) the consideration for all the gambling supplies made by the registered person in the accounting period; and

(ii) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሠ) በተተረጎመው መሠረት በገንዘብ ሽልማቶች ውስጥ ከተጠቃለለው ሂሳብ ውስጥ በተያዘው የሂሳብ ጊዜ ወይም ባለፈው የሂሳብ ጊዜ ከተሰረዘው የገንዘብ መጠን ውስጥ የተመዘገበው ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ መልሶ የሰበሰበው የገንዘብ መጠን፤

ሠ) "ጠቅላላ የገንዘብ ሽልማት" ማለት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የዕድል ሙከራ ውርርድ፤ የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ወይም የዕድል ሙከራ ጨዋታ ኪሣራ የነበረ ቢሆንም ባይሆንም የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ያረጋጠመው የሚከተለው ሁኔታ ነው፦

(i) በእድል ሙከራ ጨዋታ ውጤት መሠረት የተመዘገበው ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ የከፈለው የጥሬ ገንዘብ ሽልማት፤

(ii) የተመዘገበው ሰው የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ተሳታፊዎች ካጋጠማቸው ኪሳራ ውስጥ የተወሰነውን መልሶ እንዲከፍል በመካከላቸው የነበረው ውል የሚያስገድድ በመሆኑ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ለዕድል ሙከራ ጨዋታ ተሳታፊዎች የከፈለው ገንዘብ፤

(iii) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የገንዘብ መጠን (ካለ)፣ በቀዳሚው የሂሳብ ጊዜ አጋጥሞ ከሆነ እና

(iv) የተመዘገበው ሰው ያልተሰበሰበው ዕዳ ከተገባበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር ፲፪ ወር ጊዜ ውስጥ ያልሰበሰበው እና በተመዘገበው ሰው ለቀረበ ለሁሉም ወይም ለከፊል የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ሊከፈል ሲገባ ያልተከፈለ በመሆኑ ምክንያት ከሂሳብ መዝገብ የተሠረዘ ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ፡፡

(ii) any amounts recovered by the registered person in the accounting period for an amount written off in the current or a previous accounting period that were included in total monetary prizes under paragraph (d) of the definition of that term in this Sub-Article; and

e) "total monetary prizes", in relation to a registered person for an accounting period, is the sum of the following amounts, whether or not the relevant gambling event, gambling supply, or gambling loss occurred during the period:

(i) the monetary prizes paid by the registered person in the accounting period because of the outcome of gambling events;

(ii) the amount of money paid in the accounting period by the registered person to a recipient of the registered person's gambling supplies because of an agreement between them requiring the registered person to repay a proportion of the recipient's losses from those supplies;

(iii) the amount, if any, referred to in Sub-Article (3) of this Article arising in the immediately preceding accounting period; and

(iv) an amount that the person writes off as a bad debt in relation to all or a part of the consideration for a gambling supply made by the person that is due as a debt to the person and has not been received within 12 months of the debt being incurred.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) ፌደል ተራ (ሠ)ለጠቅላላ የገንዘብ ሽልማት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የተካተተው ክፍያ ለአቅርቦት የተፈፀመ ክፍያ እንዳልሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።

**፲፫. <u>የጠቅላላ መድን አቅርቦት</u>**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመድን ሰጪ ድርጅት የሚያቀርበው የጠቅላላ መድን ውል አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

፪/ መድን ገቢው ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ቢሆንም ባይሆንም፣ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም የመድን ሰጪው ላቀረበው የመድን አቅርቦት የሚከፈለው የአረቦን ክፍያ የአቅርቦቱ ዋጋ እንደሆነ ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ይደረግበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የጠቅላላ መድን አገልግሎት አቅርቦቱ የተከናወነው ለተመዘገበ ሰው በሚሆንበት ጊዜ እና አገልግሎቱን ተጠቅሞ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ከሆነ፣ የተመዘገበው ሰው በአረቦኑ ላይ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በግብአት ታክስነት የማቀናነስ መብት ይኖረዋል፡፡

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተፈፃሚ የሚሆነው ለታክሱ ለተመዘገበ ሰው በሚከፈለው የመድን ካሳ ክፍያ ላይ ብቻ ነው፡፡

፭/ ለአዋጁ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ከመድን ሰጪው የመድን ካሳ በሚከፈለው ጊዜ፣ የካሳ ክፍያው መድን ሰጪው ለመድን ተቀባዩ ላቀረበው አገልግሎት የተከፈለ ዋጋ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም የካሳ ክፍያ የተከፈለው ለታክሱ የተመዘገበ ሰው በአቅርቦቱ ላይ የሚከፈለውን ታክስ የመሰብሰብ እና ለታክስ ባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

4/ A payment referred to in the definition of "total monetary prizes" in Sub-Article (3) of this Article shall be treated as if it were not consideration for a supply.

**13. <u>Provision of General Insurance</u>**

1/ Subject to the provisions of Article 40 Sub-Article (2) of the Proclamation, the tax shall apply to the supply of general insurance contracts provided by insurance companies.

2/ For the purposes of Sub-Article (1) of this Article, regardless of whether the insured is a tax-registered person, the premium paid for insurance provided by the insurer shall be deemed the value of the service provided and shall be subject to tax.

3/ When general insurance services are provided to a registered person according to Sub-Article (2) of this Article who uses the service to carry out taxable activities, the registered person is entitled to credit the tax paid on the premium as input tax.

4/ Article 40 Sub-Article (1) of the Proclamation applies exclusively to the payment of insurance compensation to a person registered for tax.

5/ For the implementation of Article 40 Sub-Article (1) of the Proclamation, when an insurer pays insurance compensation to a tax-registered person, the compensation is considered as the price paid by the insurer for the services provided to the insured. Therefore, the tax-registered person receiving the compensation is required to collect the VAT due on the supply and report it to the tax authority.

፮/ በአዋጁ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት መድን ሰጪው ለተመዘገበው የመድን አገልግሎት ተጠቃሚ የሚከፍለው የካሳ ክፍያ የተጨማሪ እሴት ታክሱን ያካተተ ተደርጎ ስለሚቆጠር መድን ገቢው የሚከፍለው የውጤት ታክስ መጠን ከታክስ ማስከፈያ መጣኔው ጋር እኩል ነው፡፡

፯/ በሀገር ውስጥ የተመዘገበ የጠለፋ መድን ሰጪ ኩባንያ ለጠለፋ መድን አቅርቦት የሚያስከፍለው አረቦን እና በጠለፋ መድን ውሉ መሰረት የሚከፍለው የካሳ ክፍያ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች የሚከተል ይሆናል፡፡

፰/ የጠለፋ መድን ሰጪ ኩባንያው በሀገር ውስጥ ያልተመዘገበ በሚሆንበት ጊዜ፣ የተጨማሪ እሴት ታክሱ በአዋጁ አንቀጽ ፮ በተደነገገው መልኩ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፱/ በአዋጁ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት የተመዘገበው መድን ሰጪ በአጠቃላይ መድን ውል መሰረት የመዳረግ መብቱን ተጠቅሞ ለመድን ገቢው የከፈለውን ካሣ ከሌሎች አካላት መልሶ የተቀበለ እንደሆነ የተቀበለው ገንዘብ ታክስ ለሚጣልበት የመድን አገልግሎት እንደተከፈለ ክፍያ ተቆጥሮ በተከፈለው የካሳ ክፍያ ውስጥ የታክስ ክፍልፋይ መጠኑ እንደ ውጤት ታክስ ይቆጠራል፡፡

፲/ የእስልምና ኢንሹራንስ በአዋጁ ለረጅም ጊዜ መድን በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈን ከሆነ ከታክሱ ነፃ ይሆናል፡፡

፲፩/ የመድን ረዳቶች በአጠቃላይ ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የሚከፈል የኮሚሽን ክፍያ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

6/ The compensation paid by the insurer to the registered insured, according to Article 40 Sub-Article (1) of the Proclamation and Sub-Article (4) of this Article, is considered to include VAT, meaning the amount of output tax paid by the insured equals the amount of the tax bill.

7/ VAT applicable to the premium charged by a domestically registered re-insurance company for providing re-insurance, and to the compensation paid under the re-insurance contract, shall be subject to the provisions of this Article.

8/ If the re-insurance company is not registered in the country, VAT shall be applied as stipulated in Article 6 of the Proclamation.

9/ In accordance with Article 40 Sub-Article (6) of the Proclamation, the amount received by the registered insurer for acting under the general insurance contract and receiving compensation paid to the insured from other parties by subrogation shall be considered as payment for taxable insurance services, and the tax fraction of the compensation paid shall be considered as tax.

10/ Islamic insurance shall be exempt from VAT, provided that it falls within the scope of the definition of long-term insurance as stipulated in the Proclamation.

11/ VAT shall apply to the commission paid to insurance assistants for the services they provide.

፲፪/ ለአዋጁ እና ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) አፈፃፀም "የመድን ረዳቶች" የሚባሉት በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጣቸው የመድን ወኪሎች፣ የመድን ደላሎች፣ የጉዳት ገማቾች እና የመድን መርማሪዎች ናቸው፡፡

**፲፬. <u>በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርብ የትራንስፖርት አገልግሎት</u>**

፩/ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በዲጂታል መንገዶች (ከዚህ በኋላ "ፕላትፎርም" እየተባለ በሚጠራው) የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን በሚመለከት ነው፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ፕላትፎርም አቅራቢ" ማለት የመንገደኞችን የትራንስፖርት አገልግሎት በማመቻቸት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መንገደኞችን ከትራንስፖርት አቅራቢዎች ጋር የሚያገናኝ ማንኛውም ሰው ነው።

፫/ በፕላትፎርም አቅራቢ በኩል የሚመቻች የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን በተመለከተ ፕላትፎርም አቅራቢው ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦትን እንዳከናወነ ተደርጎ ይወሰዳል።

፬/ የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት የተከናወነበት ቦታ የሚባለው አገልግሎቱ በሚሰጥበት ጊዜ ተሳፋሪው የሚገኝበት ቦታ ነው።

፭/ ማናቸውንም ክፍያዎችን እና ኮሚሽኖችን ጨምሮ ሌሎች ተሳፋሪው ከሚከፍላቸው ጠቅላላ ክፍያዎች ላይ የፕላትፎርሙ አቅራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስን መሰብሰብ አለበት።

፮/ የፕላትፎርም አቅራቢው በየእለቱ መጨረሻ ለመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

12/ For the purposes of the Proclamation and Sub-Article (11) of this Article, "insurance assistants" shall refer to insurance agents, insurance brokers, loss assessors, and insurance valuators licensed by the National Bank.

**14. <u>Transport Service Provided by Electronic Means</u>**

1/ This provision shall apply to the provision of transport services facilitated by digital means (hereinafter referred to as the "Platform") within the territory of Ethiopia.

2/ For the purposes of this Article, a "Platform Provider" is any person who facilitates passenger transport services by connecting passengers with transport providers through electronic means.

3/ With respect to passenger transport services facilitated by the platform provider, the platform provider is deemed to have made a taxable supply.

4/ The location where the passenger transport service is provided shall be considered the place where the passenger is at the time the service is provided.

5/ The platform provider shall collect VAT on the total fees paid by the passenger, including any fees and commissions.

6/ The platform provider must issue a VAT invoice to the passenger transport service provider at the end of each day.

፯/ ፕላትፎርም አቅራቢው የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ በተደነገገው ጊዜ እና አሰራር መሰረት ለታክስ ባለስልጣኑ ማስተላለፍ አለበት።

፰/ ፕላትፎርም አቅራቢው አገልግሎት የተሰጠበትን ቀን፣ ሰዓት፣ ቦታ፣ የክፍያ መጠን እና የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ሁሉንም የመንገደኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ አለበት።

፱/ ፕላትፎርም አቅራቢው በአዋጁ መሰረት ተገቢውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

፲/ በአዋጁ በተመለከተው አጠቃላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ አሰራር ሥርዓት መሰረት የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢው ከመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት ጋር በቀጥታ ለተያያዙ ግዥዎች የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፲፩/ ፕላትፎርም አቅራቢው በመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢዎች ምትክ ታክሱን የመሰብሰብ እና የማስተላለፍ ኃላፊነት ቢኖርበትም፣ የትራንስፖርት አቅራቢዎች ዓመታዊ የሽያጭ መጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ የተቀመጠውን የገንዘብ ገደብ የሚያሟላ ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ አለባቸው።

፲፪/ የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ፕላትፎርምን ሳይጠቀሙ ለሚሰጡት ለእያንዳንዱ የትራንስፖርት አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ የመሰብሰብ እና ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

7/ The platform provider must remit the VAT collected to the tax authority according to the time and procedure stipulated in the Proclamation.

8/ The platform provider must maintain detailed records of the passenger transport services, including date, time, location, fees, and VAT.

9/ The platform provider must submit the appropriate VAT return to the tax authority in accordance with the Proclamation.

10/ According to the general VAT deduction system, the passenger transport service provider may claim a deduction of the input tax paid on purchases directly related to the provision of passenger transport services.

11/ Notwithstanding the fact that Although the platform provider is responsible for collecting and remitting the tax on behalf of passenger transport service providers, transport providers must register for VAT if their annual sales volume meets the financial threshold for VAT registration.

12/ Passenger transport service providers are required to collect and invoice VAT for each transport service they provide independently of the platform.

## ክፍል አራት

## የግብአት ታክስን ስለማቀናነስ እና ስለ ተመላሽ

**፲፭. ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በሚጀመርበት ወይም በሚቋረጥበት ቀን የግብአት ታክስን ስለማቀናነስ**

የታክስ ማቀናነስ በሚፈቀድለት ግዥ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የሚፈፀመው የታክስ ማቀናነስ ሂደት የታክስ ማቀናነስ በሚፈቀድለት ግዥ በአዋጁ መሠረት ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በሚጀመርበት ወይም በሚቋረጥበት ቀን የሚከናወን የግብአት ታክስ ማቀናነስ አሰራር ከግምት ውስጥ ያሰገባ መሆን አለበት።

**፲፮ የግብአት ታክስ ተቀናሽን ስለመከልከል**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ(ሀ) የተደነገገው ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ የንግድ ወይም ሌሎች የጭነት መኪናዎችን እና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን አይመለከትም።

፪/ በአዋጁ አንቀፅ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንገደኛ ተሽከርካሪዎች ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ወይም ከትራንስፖርት ንግድ አገልግሎት ውጪ የዋሉ በሚሆንበት ጊዜ ለእነዚህ ተሽከርካሪዎች ለተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡

**፲፯. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽን ስለመክፈል**

በአዋጁ ክፍል አስር በተመለከተው መሠረት የተመዘገበው ሰው ተመላሽ ሊከፈለው በሚገባ በማናቸውም የሂሳብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ሆኖ ከተገኘ የታክሱ ባለሥልጣን የተመዘገበው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳያስታውቅ ለቆየበት የሂሳብ ጊዜ ሁሉ የማስታወቅ ግዴታውን እስከሚወጣ ድረስ ተመላሹ ገንዘብ ሳይከፈለው እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል።

## PART FOUR

## INPUT TAX CREDITS AND REFUNDS

**15. Input Tax Credits on Commencement or Termination of a Taxable activity**

The input tax payable on a creditable acquisition in commencing or terminating a taxable activity shall be taken into account in calculating the input tax credits allowed under the Proclamation for the accounting period in which the creditable acquisition occurred.

**16. Denial of Input Tax Credits**

1/ Article 30 Sub-Article (1) Paragraph (a) of the Proclamation shall not apply to a commercial truck or other vehicle designed and used primarily for the carriage of goods or a bus used as a public mass transit vehicle.

2/ Subject to Article 30 Sub-Article (1) paragraph (a) of the Proclamation, when passenger vehicles are removed used other than for the transport business, input tax shall not be deducted for the VAT paid on these vehicles.

**17. Payment of VAT Refunds**

Where, at the time that a registered person is entitled to a refund under Part Ten of the Proclamation, the person has failed to file a VAT return for any accounting period, the Tax Authority may withhold payment of the refund until the registered person has filed all outstanding VAT returns.

**፲፰. <u>ለተመላሽ ስለሚያዝ ገንዘብ</u>**

የታክሱ ባለሥልጣን ለተመላሽ ክፍያ እንዲያውለው ከጠቅላላ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተሰብሳቢ ገንዘብ ላይ በታክሱ ባለሥልጣን ተቀናሽ ተደርጎ የሚያዘው መቶኛ መጠን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች</u>

**፲፱. <u>ቀለል ያለ የታክስ ደረሰኝ የሚሰጥበት ሁኔታ</u>**

በአዋጁ አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተደነገገው መሠረት ቀለል ያለ ደረሰኝ የሚሰጠው ከብር ፲ሺ (አስር ሺህ ብር) ላልበለጠ ግዥ ነው።

**፳. <u>የታክስ ደረሰኝ ይዘት</u>**

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) አፈጻጸም የታክስ ደረሰኝ እና ቀለል ያለ የታክስ ደረሰኝ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዙ ይገባል፦

ሀ) ግልፅ በሆነ ቦታ “የታክስ ደረሰኝ “ የሚል ጽሑፍ፤

ለ) የአቅራቢው ስም፤ አድራሻ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

ሐ) የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፤ አድራሻ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

መ) የታክስ ደረሰኙ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፤

ሠ) ስለዕቃው መግለጫ (ብዛቱን እና መጠኑን ጨምሮ) ወይም የተሰጠውን አገልግሎት፤ እና

ረ) ለአቅርቦቱ የተከፈለውን ዋጋ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን፡፡

**18. <u>Amount to be retained for Refunds</u>**

The percentage of funds to be retained by the tax authority from the total amount of collected Value Added Tax for the purpose of facilitating refunds shall be determined in accordance with the directive issued by the Ministry of Finance.

## <u>PART FIVE</u>

## <u>VAT DOCUMENTATION</u>

**19. <u>When a Simplified Tax Invoice Can be Provided</u>**

The amount specified for the purposes of Article 52 Sub-Article (3) of the Proclamation is 10,000 birr.

**20. <u>Contents of Tax Invoices</u>**

1/ For the purposes of Article 52 Sub-Article (5) of the Proclamation, a tax invoice and simplified tax invoice shall contain the following particulars:

a) the words “TAX INVOICE” in a prominent place;

b) the name, address, TIN, and VAT registration number of the supplier;

c) the name, address, TIN, and, if registered, the VAT registration number of the recipient of the supply;

d) the individualised serial number and the date on which the tax invoice is issued;

e) the description of the goods (including quantity or volume) or services supplied; and

f) the consideration for the supply and the amount of VAT charged.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገበው ሰው አቅርቦቱን የሚፈጽመው በመሣሪያ፣ በቆጣሪ ወይም በሌላ በሳንቲም፣ በገንዘብ ወካይ ነገር ወይም በዴቢት ወይም ክሬዲት ካርድ ከሆነ፣ መሣሪያው፣ ቆጣሪው ወይም ገንዘብ መቀበያው ማሽን፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ ቀለል ያለ ደረሰኝ ለአቅርቦቱ ተቀባይ መስጠት አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው መሣሪያው፣ ቆጣሪ ወይም ገንዘብ መቀበያ ማሽን የታክስ ደረሰኝ ለመስጠት የማይችል ከሆነ የተመዘገበው ሰው በየቀኑ በመሳሪያው፣ በቆጣሪው ወይም በገንዘብ መቀበያው ማሽን የተከናወነውን ግብይት የሚያሳይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን መረጃ በመያዝ በቀኑ መጨረሻ የታክስ ደረሰኝ መቁረጥ አለበት።

፬/ ለአዋጁ አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) አፈፃፀም በአቅርቦት ተቀባዩ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

ሀ) በሚታይ ቦታ ላይ “በአቅርቦት ተቀባይ የተዘጋጀ የታክስ ደረሰኝ” የሚል ጽሑፍ፣

ለ) አቅርቦት ተቀባዩ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ተቀባይ ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣

ሐ) የአቅራቢው ስም እና አድራሻ፣

መ) በአቅርቦት ተቀባዩ የተዘጋጀው የታክስ ደረሰኝ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፣

ሠ) የተሰጠው አገልግሎት መግለጫ፣ እና

ረ) ለአቅርቦቱ የተከፈለው ዋጋ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ፡፡

2/ Subject to Sub-Article (4) of this Article, where a registered person makes a taxable supply through a machine, meter, or other device operated by a coin, note, token, or credit or debit card, the machine, meter, or device shall make a simplified tax invoice containing the particulars specified in Sub-Article (1) of this Article available to the recipient of the supply.

3/ If a machine, meter, or other device referred to in Sub-Article (2) of this Article does not have the capacity to provide a tax invoice, the registered person shall keep a daily record of the information specified in Sub-Article (2) of this Article in relation to taxable supplies made through the machine, meter, or other device during the day.

4/ For the purposes of Article 52 Sub-Article (4) of the Proclamation, a recipient-created tax invoice shall contain the following particulars:

a) The words “RECIPIENT-CREATED TAX INVOICE” in a prominent place;

b) the name, address, TIN, and VAT registration number of the recipient of the reversed charged supply;

c) the name and address of the supplier;

d) the individualised serial number and the date on which the recipient-created tax invoice is created;

e) the description of the services supplied; and

f) the consideration for the supply and the amount of VAT charged.

## ፳፩. የዴቢት ሰነድ እና የክሬዲት ሰነድ ይዘት

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃፀም የክሬዲት ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፦

ሀ) በሚታይ ቦታ ላይ "የክሬዲት ሰነድ" የሚል ጽሁፍ፤

ለ) የአቅራቢው ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

ሐ) የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

መ) የክሬዲት ሰነዱ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፤

ሠ) ክሬዲት ሰነዱ የተሰጠበትን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ለይቶ ማወቅ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መረጃን ጨምሮ፣ የክሬዲት ሰነድ ለመስጠት ምክንያት የሆነውን የሚያስረዳ አጭር መግለጫ፤ እና

ረ) በታክስ ደረሰኙ የተመለከተው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ ትክክለኛው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ በእነዚህ ሁለት ዋጋዎች መካከል ያለው ልዩነት፣ እና በልዩነቱ ላይ የሚታሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን።

፪/ ለአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃፀም የዴቢት ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፦

ሀ) በሚታይ ቦታ ላይ "የዴቢት ሰነድ" የሚል ጽሑፍ፤

ለ) የአቅራቢው ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

ሐ) የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

## 21. Contents of Credit Notes and Debit Notes

1/ For the purposes of Article 53 Sub-Article (3) of the Proclamation, a credit note shall contain the following particulars:

a) the words "CREDIT NOTE" in a prominent place;

b) the name, address, TIN, and VAT registration number of the supplier;

c) the name, address, TIN, and VAT registration number of the recipient, if registered for VAT;

d) the individualised serial number and the date on which the credit note is issued;

e) a brief description of the circumstances giving rise to the issuing of the credit note, including information sufficient to identify the taxable supply to which the credit note relates; and

f) the consideration shown on the tax invoice for the supply, the correct amount of the consideration, the difference between those two amounts, and the amount of VAT that relates to the difference.

2/ For the purposes of Article 53 Sub-Article (3) of the Proclamation, a debit note shall contain the following particulars:

a) the words "DEBIT NOTE" in a prominent place;

b) the name, address, TIN, and VAT registration number of the supplier;

c) the name, address, TIN, and VAT registration number of the recipient, if registered for VAT;

መ) የዴቢት ሰነዱ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፤

ሠ) ዴቢት ሰነዱ የተሰጠበትን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ለይቶ ማወቅ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መረጃን ጨምሮ፣ የዴቢት ሰነድ ለመስጠት ምክንያት የሆነውን የሚያስረዳ አጭር መግለጫ፣ እና

ረ) በታክስ ደረሰኙ የተመለከተው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ ትክክለኛው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ በእነዚህ ሁለት ዋጋዎች መካከል ያለው ልዩነት፣ እና በልዩነቱ ላይ የሚታሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን::

## ክፍል ስድስት

## በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ ስለመጠቀም

### ፳፪. የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ

፩/ ለዚህ የደንቡ ክፍል አፈጻጸም “የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ” ማለት የሽያጭ እና ተያያዥነት ያለውን መረጃ ለመመዝገብ እና ለማስተላለፍ የሚያግዝ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ነው።

፪/ የተመዘገበው ሰው የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ የሚጠቀምበት ሶፍትዌር በታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደ መሆን አለበት።

፫/ የተመዘገበው ሰው የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያን ጥቅም ላይ ከማዋሉ ፯ ቀን በፊት በእያንዳንዱ የንግድ ስራው ቦታ የሚጠቀምበትን መሳሪያ እና ሶፍትዌር ዝርዝር ባህሪያት ለታክሱ ባለሥልጣን በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት። የታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቂያው በደረሰው በሰባት (፯) ቀናት ውስጥ ሶፍትዌሩ ከዚህ ደንብ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የሚገልፅ ማረጋገጫ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተውን ማስታወቂያ ለታክስ ባለሥልጣኑ የሚያቀርበው የተመዘገበ ሰው በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያው ለመጠቀም የተመዘገበ ሰው መሆን አለበት።

d) the individualised serial number and the date on which the debit note is issued;

e) a brief description of the circumstances giving rise to the issuing of the debit note, including information sufficient to identify the taxable supply to which the debit note relates; and

f) the consideration shown on the tax invoice for the supply, the correct amount of the consideration, the difference between those two amounts, and the amount of VAT that relates to the difference.

## PART SIX

## USE OF ELECTRONIC FISCAL DEVICES

### 22. Electronic Fiscal Device

1/ In this Part: “electronic fiscal device” means an electronic device for recording and transmitting sales and related data.

2/ The software for an electronic fiscal device must be approved by the Tax Authority.

3/ A registered person shall notify the Tax Authority, in writing, of the details of the electronic fiscal device and software for such device used at each place of business at least 7 days prior to the device coming into use. The tax authority shall provide the taxpayer with a certificate stating that the software complies with this regulation within seven (7) days of receipt of the notice.

4/ A registered person who has notified the Tax Authority in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall be the registered user of the electronic fiscal device.

**፳፫. <u>በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ ስለመጠቀም</u>**

የተመዘገበ ሰው በዚህ የደንቡ ክፍል በተዘረዘረው መሰረት በእያንዳንዱ የንግድ ስራ በሚያከናውንበት ቦታ በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ መጠቀም አለበት።

**፳፬. <u>የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሣሪያ ተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር</u>**

የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

፩/ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረብ ጋር ግንኙነት ሊኖረው የሚችል መሆን አለበት፤

፪/ መረጃዎችን በበቂ ሁኔታ መያዝ የሚያስችል ማከማቻ ሊኖረው ይገባል፤

፫/ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፸፯ በተመለከተው የታክስ ህግ የስራ ቋንቋ መልዕክቶችን ማሳየት የሚችል መሆን አለበት፤

፬/ ደህንነቱ የተጠበቀ፤ በቀላሉ ሊለወጥ እና ጉዳት ሊደርስበት የማይችል ሊሆን ይገባል፤

፭/ የሚከተሉትን የሚያከናውን ሊሆን ይገባል:-

(i) ለደንበኞች የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኞችን ማተም ወይም የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኞችን ማስተላለፍ የሚችል፤

(ii) ከታክስ ባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርአት ጋር መጣጣም የሚችል፤

(iii) በውስጡ የተመዘገበውን መረጃ ለታክሱ ባለስልጣን ማስተላለፍ የሚችል ወይም ከታክሱ ባለስልጣን መሳሪያ ጋር መገናኘት የሚችል፤

(iv) በታክስ ህጎች ላይ የሚደረገውን ለውጥ ተከትሎ ወቅታዊ ሊደረግ የሚችል፤ እና

(v) በዚህ የደንቡ ክፍል የተዘረዘሩ መረጃዎችን መያዝ የሚችል፡፡

**23. <u>Use of Electronic Fiscal Device</u>**

A registered person shall use an electronic fiscal device at each place of business of the person in accordance with this Part.

**24 .<u>Specifications of an Electronic Fiscal Device</u>**

An electronic fiscal device shall satisfy the following requirements:

1/ be capable of interconnectivity with information technology networks;

2/ have sufficient storage to maintain records;

3/ display clear messages in the working language of the tax laws as specified in Article 77 of the Tax Administration Proclamation;

4/ be secure and tamperproof;

5/ be capable of:

(i) printing tax invoices for, or transmitting tax invoices to, customers;

(ii) integrating with the Tax Authority’s information technology system;

(iii) transmitting, or connecting to a device that will transmit, the recorded data to the Tax Authority;

(iv) Allowing updates for changes in the tax laws; and

(v) Capturing the information required under this Part.

**፳፭. <u>የተመዘገቡ ተጠቃሚዎች ግዴታ</u>**

፩/ የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ ተጠቃሚ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) እያንዳንዱን የሚፈፅመውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሣሪያን በመጠቀም መመዝገብ አለበት፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእያንዳንዱ ለሚፈፅመው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያን በመጠቀም የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፤ እና

ሐ) የሚሰጠው የታክስ ደረሰኝ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት፤

፪/ በአንድ ግብይት ከአንድ በላይ የሆኑ እቃዎች እና አገልግሎቶች አቅርቦት የሚፈጸም ከሆነ፤ አቅርቦቱ የሚያካትታቸውን እቃዎች እና አገልግሎቶች በመዘርዘር አንድ ደረሰኝ ብቻ መስጠት ይቻላል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልባቸው በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱ እቃዎች በደረሰኙ ውስጥ ተለይተው መታየት አለባቸው።

፬/ የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ተጠቃሚ፡-

ሀ) ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦቱ ተቀባይ የኤሌክትሮክ የታክስ ደረሰኝ መስጠት ወይም ማስተላለፍ፤ እና

ለ) በዚህ ደንብ መሠረት የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኙን ለታክሱ ባለሥልጣን መላክ ወይም ማስተላለፍ አለበት።

፭/ በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ መጠቀም የሚችለው በመሳሪያው ለመጠቀም የተመዘገበ ተጠቃሚ ብቻ ነው። የገቢዎች ሚኒስቴር በኤሌክትሮኒክስ የፊስካል መሣሪያ ለመጠቀም የሚመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ሊከተሉት የሚገባውን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

**25. <u>Obligations of Registered Users</u>**

1/ A registered user of an electronic fiscal device shall ensure that:

a) each taxable supply made by the user is recorded using the electronic fiscal device;

b) subject to Sub-Articles (2) and (3) of this Article, a tax invoice is generated by the electronic fiscal device in respect of each taxable supply made by the user; and

c) The tax invoice contains the information specified in Article 20 of these Regulations.

2/ Where multiple goods or services are supplied as part of a transaction, a single tax invoice can be provided itemising the goods or services supplied.

3/ Where Sub-Article (2) of this Article applies, any itemised supplies in respect of which no VAT is payable must be identified on the invoice.

4/ A registered user of an electronic fiscal device shall:

a) transmit or deliver the tax invoice for a taxable supply to the recipient of the supply; and

b) Transmit or deliver the tax invoice details to the Tax Authority.

5/ An electronic fiscal device shall be used only by the registered user of the device. The Ministry of Revenues shall issue a directive determining the procedures to be followed by taxpayers who register to use the electronic fiscal device.

**፳፮. በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ መገልገል አለመቻል**

፩/ የተመዘገበ ተጠቃሚ በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው የኤሌክትሪክ አቅርቦት በሌለ ጊዜም ያለማቋረጥ መጠቀም እንዲችል ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ አለበት።

፪/ የተመዘገበው ተጠቃሚ በማናቸውም ምክንያት በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው መጠቀም ያልቻለ እንደሆነ፦

ሀ) በመሣሪያው መጠቀም እንዳይችል ያደረገው ሁኔታ በተፈጠረ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፤

ለ) በመሣሪያው መጠቀም ባልቻለበት ጊዜ ውስጥ ያከናወነውን አቅርቦት በማናቸውም ሌላ ዘዴ መመዝገብ፤ እና

ሐ) በመሣሪያው መጠቀም ባልቻለበት ጊዜ ውስጥ ላከናወነው ግብይት ለአቅርቦቱ ተቀባይ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚመርጠው የማተሚያ ድርጅት የታተመ በእጅ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

፫/ የተመዘገበው ተጠቃሚ በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያው መጠቀሙን ሲቀጥል፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) መሰረት ያከናወነውን አቅርቦት በዝርዝር በመሣሪያው ውስጥ መመዝገብ አለበት።

**፳፯. የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ዝግጁነት**

፩/ የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሣሪያ የተመዘገበ ተጠቃሚ፦

ሀ) የሽያጭ ተግባር በሚያከናውንባቸው ቦታዎች ሁሉ የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሣሪያ እንዲኖር ማድረግ፤

ለ) የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሣሪያዎችን ለመቆጣጠር የተመደቡ ሰራተኞች ስራቸውን እንዲያከናውኑ ማገዝ፤

**26. Inability to use Electronic Fiscal Devices**

1/ The registered user of an electronic fiscal device shall take reasonable measures to ensure continuity of operations of the device if there is an interruption of the power supply to the device.

2/ Where a registered user cannot use an electronic fiscal device for any reason, the registered user shall:

a) Notify the Tax Authority, in writing, within 24 hours of the occurrence of the registered user's inability to use the device;

b) Record supplies made during the period of the interruption in any other manner as specified by the Tax Authority; and

c) Provide a recipient of a taxable supply made during the period of the interruption with a manually prepared tax invoice.

3/ Once the registered user is again able to use the electronic fiscal device, the registered user shall enter into the device details of the supplies referred to in Sub-Article (2) paragraph (b) of this Article.

**27. Readiness of Electronic Fiscal Devices**

1/ A registered user of an electronic fiscal device shall:

a) ensure that the device is available for use at the point of sale;

b) facilitate the inspection of the device by a tax officer authorised to inspect electronic fiscal devices;

ሐ) መሣሪያው ሁል ጊዜም ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን ወቅታዊ የሆነ ዕድሳት እንዲደረግለት ማድረግ፤

መ) የተመዘገበው ተጠቃሚ ለሚጠቀምበትየኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ(ዎች) የተደረገውን ዕድሳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ፤ የሚያሳይ መዝገብ ማቋቋም እና ጠብቆ ማቆየት፦

(i) የመሣሪያውን ዕድሳት ስራ ያከናወነውን ሰው ስም እና አድራሻ፤ እና

(ii) የመሣሪያውን ዕድሳት ስራ ባከናወነው ሰው ፊርማ የተረጋገጠ በእያንዳንዱ ዕድሳት በተደርገበት ጊዜ የተከናወነውን ዕድሳት የሚያሳይ ዝርዝር፤ እና

ሠ) የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዘሩ ሌሎች ተፈላጊ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት።

፪/ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያውን እድሳት የሚያከናውነው ሰው የመስሪያውን አሰራር ለመለወጥ የተከናወነ ተግባር መኖሩን ሲደርስበት ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

**፳፰. <u>በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሣሪያ መጠቀምን ስለማቋረጥ</u>**

፩/ የተመዘገበ ሰው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ መጠቀምን ማቋረጥ ከፈለገ ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት፦

ሀ) የተጠቃሚው የንግድ ስራ ከተዘጋ፤

ለ) ታክስ የሚከፈልባቸውን አቅርቦቶች ማከናወን ካቆመ፤

ሐ) ሌሎች ምክንያቶች ካሉ፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርበው ማስታወቂያ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ መጠቀም ከመቋረጡ ከ፴ ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን መቅረብ አለበት።

c) ensure that the device is regularly serviced to ensure the proper functioning of the device at all times;

d) keep and maintain a ledger in which a record of the servicing of the registered user's electronic fiscal device (or devices) is recorded specifying:

(i) the name and address of the person servicing the device; and

(ii) an entry for each time the device is serviced describing the service and signed by the person servicing the device; and

e) Comply with such requirements as may be specified in a Directive issued by the Ministry of Revenue.

2/ A person servicing an electronic fiscal device shall report to the Tax Authority if there is evidence that the device has been tampered with.

**28. <u>Discontinuing Use of an Electronic Fiscal Device</u>**

1/ A registered user shall notify the Tax Authority if the user intends to discontinue use of an electronic fiscal device due to:

a) The closure of the user's business;

b) Cessation of the making of taxable supplies; or

c) Any other reason.

2/ A notification under Sub-Article (1) of this Article shall be in the approved form and lodged with the Tax Authority within 30 days prior to discontinuation of the use of the electronic fiscal device.

፫/ የተመዘገበው ተጠቃሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቂያ ካቀረበ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቂያ በቀረበ በ፳፩ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያውን አገልግሎት ማቋረጥ አለበት። የታክሱ ባለስልጣን በ፳፩ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ በመሳሪያው መጠቀም እንደተቋረጠ ይቆጠራል፡፡

**፳፱. <u>በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ የሚዘጋጅ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነድ</u>**

በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሣሪያ የሚዘጋጅ የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ኖት እና የዴቢት ኖት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

፩/ እንደሁኔታው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ እና ፳ የተዘረዘሩትን መረጃዎች፣

፪/ የመሣሪያውን የተለየ መለያ፣

፫/ እንደአግባብነቱ የታክስ ደረሰኙን፣ የክሬዲት ኖቱን ወይም የዴቢት ኖቱን የተለየ መለያ፣

፬/ የፈጣን ምላሽ (ፈ.ም) ኮድ፣ እና

፭/ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዝራቸው ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፡፡

**፴. <u>የመረጃ ደህንነት እና መረጃን ስለማስተላለፍ</u>**

የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሣሪያ የሚከተሉትን ማከናወን የሚችል መሆን አለበት፦

፩/ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት እና የዴቢት ኖት መረጃዎችን እንዲሁም የየእለቱን መጨረሻ የማጠቃለያ መረጃ የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሠረት ወደታክስ ባለሥልጣኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ማስተላለፍ፣

፪/ በውስጡ የተከማቸውን መረጃ ማተም እና መስጠት፣

፫/ በውስጡ የያዘውን መረጃ ለማየት ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ሊረዱት በማይችል አኳኋን መረጃን በውስጡ ማከማቸት፣

፬/ በውስጡ ያለው መረጃ አስተማማኝ መሆን፣

፭/ የተፈቀደላቸውን ሰዎች ማንነት ማረጋገጥ የሚችል፣

3/ Where a registered user has lodged a notification with the Tax Authority under Sub-Article (2) of this Article, the Tax Authority may, by notice in writing and within 21 days of the notice being lodged, retire the electronic fiscal device. If the tax authority does not respond within 21 days, the use of the device will be deemed terminated.

**29. <u>VAT Documentation Generated by an Electronic Fiscal Device</u>**

A tax invoice, credit note, or debit note generated by an electronic fiscal device shall contain:

1/ The information specified in Article 19 and 20 of these Regulations, as the case may be;

2/ The unique identifier of the device;

3/ The unique identifier of the tax invoice, credit note, or debit note, as the case may be;

4/ A quick response (QR) code; and

5/ Such other information as may be required by the Tax Authority as specified in a Directive.

**30.<u>Security and Transmission of Data</u>**

An electronic fiscal device shall be capable of the following:

1/ Transmitting to the Tax Authority's information technology system tax invoice and credit and debit note data, and the end of day summary of the day's data in the manner specified in a Directive issued by the Tax Authority;

2/ Printing and providing stored data;

3/ Storing data in an unintelligible form to persons not authorised to access it;

4/ Maintaining the integrity of the data;

5/ Securing authentication for authorised users

፮/ በመሣሪያው የተከናወኑ ተግባራትን በሙሉ መዝግቦ የሚይዝ፤

፯/ ለእያንዳንዱ የታክስ ደረሰኝ የተለየ መለያ መስጠት የሚችል፡፡

## ክፍል ሰባት
## አስተዳደራዊ እና የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች

### ፴፩. በአበዳሪዎች የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ

፩/ ይህ የደንቡ ክፍል ለአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ትክክለኛ አፈፃፀም የሚያገለግል ነው።

፪/ የተመዘገበ ሰው ቢሆንም ባይሆንም በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት አበዳሪው ለሽያጭ የሚያቀርበውን የባለዕዳውን ዕቃ በሚመለከት የሚቀርበው የታክስ ማስታወቂያ በፀደቀው ቅፅ መቅረብ ያለበት ሲሆን፤ የሚከተለውን መረጃ ጭምር ሊይዝ ይገባል፡-

ሀ) የአበዳሪውን ስም፤ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሁም የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥሩን፤

ለ) የባለዕዳውን ስም፤ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሁም የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥሩን፤

ሐ) የዕቃው አቅርቦት የተፈጸመበትን ቀን፤

መ) ስለዕቃው መግለጫ እና ብዛት፤

ሠ) ለአቅርቦቱ የተፈፀመውን ክፍያ የተሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ እና

ረ) በፀደቀው ቅጽ የተመለከቱ ሌሎች መረጃዎች፡፡

፫/ አበዳሪው እና ባለዕዳው አቅርቦቱን እና በአቅርቦቱ ላይ የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ በተመለከተ በማናቸውም ታክስ በሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴያቸው ላይ ሊያቀርቡት በሚገባ የታክስ ማስታወቂያ ውስጥ ማካተት የለባቸውም።

6/ Capturing a log of all activities; and

7/ Assigning a unique identifier to each invoice.

## PART SEVEN
## ADMINISTRATIVE AND PROCEDURAL RULES

### 31. VAT Payable by Creditor

1/ This Regulation applies for the purposes of Article 42 Sub-Article (5) of the Proclamation.

2/ A return required to be filed by a creditor, whether a registered or unregistered person, under Article 42 Sub-Article (5) Paragraph (a) of the Proclamation in relation to the supply of goods by the creditor belonging to a debtor of the creditor shall be in the approved form and include the following information:

a) The creditor's name, address, and TIN, and, if registered, VAT registration number;

b) The debtor's name, address, and TIN and, if registered, VAT registration number;

c) The date of supply of the goods;

d) Adescription and quantity of the goods supplied;

e) The consideration for the supply and the amount of VAT charged on that supply; and

f) Such other particulars as may be required by the form.

3/ The creditor and debtor shall not include the supply and VAT charged on the supply in any other return required to be filed under the Proclamation or these Regulations.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ ያለበት አበዳሪ አቅርቦቱ ከተከናወነበት የሂሳብ ጊዜ መጨረሻ ባለው የመጨረሻ ቀን ወይም ከዚያ በፊት የታክስ ማስታወቂያውን ማቅረብ እና የሚፈለግበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል አለበት።

፭/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ፊደልተራ (ለ) መሠረት አበዳሪው የተበዳሪውን ዕቃ ለሽያጭ በማቅረብ ለአቅርቦቱ ተቀባይ የሚሰጠው የታክስ ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚይዝ መሆን አለበት፦

ሀ) ግልጽ በሆነ ቦታ “የታክስ ደረሰኝ” የሚል ጽሑፍ፤

ለ) የአበዳሪው ስም፤ አድራሻ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

ሐ) የተበዳሪው ስም፤ አድራሻ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

መ) የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፤ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

ሠ) አቅርቦቱ የተከናወነበት እና የታክስ ደረሰኝ የተሰጠበት ቀን፤

ረ) ስለ ዕቃው መግለጫ ( ብዛቱን እና መጠኑን ጨምሮ)፤ እና

ሰ) ለአቅርቦቱ የተፈፀመውን ክፍያ እና የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

፴፪. **<u>ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ስለሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ</u>**

፩/ ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈል ከሆነ፤ አስመጪው እቃዎቹ ወደአገር በገቡበት ጊዜ የገቢ ዕቃ ዲክላራሲዮን ለኮሚሽኑ ማቅረብ እና ወደአገር በገቡት ዕቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክሱን መክፈል አለበት።

4/ A creditor required to file a return under Sub-Article (2) of this Article shall file the return, and pay the VAT due, in relation to the supply on or before the last day of the calendar month following the end of the accounting period in which the supply occurred.

5/ A tax invoice required to be provided by a creditor under Article 42 Sub-Article (5) Paragraph (b) of the Proclamation to the recipient of a supply of the goods of a debtor shall contain the following particulars:

a) The words “TAX INVOICE” in a prominent place;

b) The name, address, and TIN and, if registered, VAT registration number of the creditor;

c) The name, address, and TIN and, if registered, VAT registration number of the debtor;

d) The name, address, and TIN of the recipient of the supply;

e) The date of the supply of the goods and the date on which the tax invoice is issued;

f) The description of the goods (including quantity or volume) supplied; and

g) The consideration for the supply and the amount of VAT charged.

32 .**<u>Collection of VAT on Imports</u>**

1/ Where VAT is payable on an import of goods, the importer shall, upon entry of the goods, furnish the Commission with an import declaration and pay the VAT due on the import.

፪/ የገቢ ዕቃ ዲክላራሲዮኑ፡-

ሀ) ኮሚሽኑ በሚወስነው ቅጽ መሆን አለበት፤

ለ) በወደአገር በገባው ዕቃ ላይ ተገቢውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማስላት የሚያስችል አስፈላጊውን መረጃ የያዘ መሆን አለበት፤ እና

ሐ) ኮሚሽኑ በሚወስነው የአቀራረብ ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት።

፫/ በአዋጅ ቁጥር ፯፻፷፰/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) በተካተተው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት የሚሸፈን ዕቃ አስመጪው በቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት የሚጠቀም ካልሆነ በስተቀር የተጨማሪ እሴት ታክስ አይከፈልበትም።

**፴፫. <u>ዘግይቶ ለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለሚቀርብ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት</u>**

በአዋጁ አንቀጽ ፳፰ መሠረት ለኮሚሽኑ ማመልከቻ የሚያቀርብ የተመዘገበ ሰው በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፷፩ መሠረት ከታክሱ ባለሥልጣን የተሰጠውን የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት በደጋፊ ማስረጃነት አያይዞ ማቅረብ አለበት።

**፴፬. <u>የአቅርቦት ተቀባዩ ላይ ታክስ ስለመወሰን</u>**

ለአዋጁ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚሰጠው የታክስ ውሳኔ የሚከተሉትን የሚይዝ መሆን አለበት፡-

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የታክስ ውሳኔ ለመስጠት ያበቃውን ምክንያት፤

፪/ በታክስ ውሳኔው መሠረት ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ በዘገየበት ሊከፈል የሚገባውን ቅጣት እና ወለድ፤ እና

፫/ የተጨማሪ እሴት ታክሱ መክፈያ ጊዜ፤ እና

2/ The import declaration shall:

a) Be in the form prescribed by the Commission;

b) State the information necessary to calculate the VAT payable in respect of the import; and

c) Be furnished in the manner specified by the Commission.

3/ Goods covered by an export trade duty incentive scheme under Proclamation No. 768/2012 (as amended) shall not be subject to VAT at the time of import, except where the importer is covered by the duty draw-back scheme.

**33 .<u>Tax Clearance Certificate for Deferred VAT</u>**

A registered person making an application to the Commission under Article 28 of the Proclamation shall include a tax clearance certificate issued by the Tax Authority under Article 61 of the Tax Administration Proclamation in support of the application.

**34 .<u>Assessment of Recipient of a Supply</u>**

For the purposes of Article 61 Sub-Article (3) of the Proclamation, an assessment raised by the Tax Authority under Article 61 Sub-Article (2) of the Proclamation shall include the following particulars:

1/ The reason for making the assessment under Article 61 Sub-Article (2) of the Proclamation;

2/ The VAT, and any late payment interest and penalty, payable under the assessment;

3/ The due date for payment of the VAT; and

፬/ በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት ቅሬታ ሊቀርብ የሚችልበትን ጊዜ፣ ቦታ እና አቀራረብ።

**፴፭. ባልተመዘገበ ሰው ላይ የሚሰጥ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ**

፩/ የታክሱ ባለስልጣን የዕቃ እና አገልግሎት አቅርቦት የሚያከናውን ያልተመዘገበ ሰው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ሊከፍል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚመለከት መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ በሚመለከት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ሊሰጥ ይችላል።

፪/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ታክስ የሚከፈልበት የዕቃ እና አገልግሎት አቅርቦት በሚያከናውን ሰው ላይ የሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የመክፈያውን ጊዜ የያዘ ማስታወቂያ ለከፋዩ ሰው መስጠት አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለከፋዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል የሚሰጠው የውሳኔ ማስታወቂያ ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም "የታክስ ውሳኔ" እንደሆነ ይቆጠራል።

## ክፍል ስምንት

## በአቅርቦት ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ መለወጥ

**፴፮. ተፈፃሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ በመለወጡ ምክንያት የአቅርቦቱ ዋጋ መለወጥ**

፩/ ማናቸውም አቅራቢ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ በውሉ ወይም በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም፣ ለአቅርቦቱ ከሚከፈለው ዋጋ በተጨማሪ የተጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከአቅርቦቱ ተቀባይ ሊጠይቅ ይችላል፡-

4/ The time, place, and manner of challenging the assessment as provided for under the Tax Administration Proclamation.

**35. Assessment of Unregistered Person**

1/ The Tax Authority may make an assessment of the amount of VAT payable by a person, not being a registered person, that supplies goods or services and represents that VAT is payable on the supply.

2/ The Tax Authority shall serve a notice of an assessment made under Sub-Article (1) of this Article on the person representing that VAT is payable on a supply of goods or services setting out the amount of VAT payable and the due date for payment.

3/ The VAT payable by a person under an assessment served on the person under this Article shall be treated as "tax" for the purposes of the Tax Administration Proclamation.

## PART EIGHT

## CHANGES IN VAT TREATMENT OF A SUPPLY

**36. Variation of Consideration on a Change in VAT Treatment**

1/ Where the following conditions are satisfied, the supplier may, despite anything to the contrary in the agreement or under any law, recover from the recipient, in addition to the consideration payable by the recipient for the supply, an amount equal to the amount of VAT imposed or the amount by which VAT was increased, as the case may be፡

ሀ) የተመዘገበ ሰው ለእቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ውል የፈረመ ከሆነ፣ እና

ለ) ውሉን ከፈረመ በኋላ በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተጣለ፡፡

፪/ ማናቸውም አቅራቢ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ በውሉ ወይም በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም፣ በአቅርቦቱ ተቀባይ ሊከፈል የሚገባውን ሂሳብ ቀሪ በተደረገው የተጨማሪ እሴት ታክስ ልክ መቀነስ አለበት፡-

ሀ) የተመዘገበ ሰው ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ውል የፈረመ ከሆነ፣ እና

ለ) ውሉን ከፈረመ በኋላ በአቅርቦቱ ላይ ተጥሎ የነበረው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተነሳ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፬) እና (፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ የተጣለ ማናቸውም አይነት ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን (በቁርጥ የሚከፈል፣ ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን ቢሆንም) ተፈጻሚ በሚሆንበት የእቃ እና አገልግሎት አቅርቦት ላይ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን እንደሁኔታው ሊከፈል በሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም በታከለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ልክ ከፍ ማለት ወይም ቀሪ በተደረገው የተጨማሪ እሴት ታክስ ልክ ዝቅ ማለት አለበት።

a) A registered person has entered into an agreement for the supply of goods or services; and

b) Subsequent to entering into the agreement, VAT is imposed on the supply, or the rate of VAT applicable to the supply, is increased.

2/ Where the following conditions are satisfied, the supplier shall, despite anything to the contrary in the agreement or under any law, reduce the amount payable by the recipient by an amount equal to the amount of VAT withdrawn;

a) A registered person has entered into an agreement for the supply of goods or services; and

b) Subsequent to entering into the agreement, the application of VAT on the supply is withdrawn.

3/ Subject to Sub-Articles (4) and (5) of this Article, if Sub-Article (1) or (2) of this Article applies in respect of a supply of goods or services that is subject to any fee, charge, or other amount (whether a fixed, maximum, or minimum fee, charge, or other amount) prescribed by, or determined pursuant to, any Proclamation, Regulation, or Directive, that fee, charge, or other amount may be increased by the amount of VAT or additional VAT chargeable, or shall be decreased by the amount of VAT no longer chargeable, as the case may be.

፬/ በማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተወሰነው ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን የተጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ወይም የተነሳውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከግምት ውስጥ ያስገባ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተፈጻሚ አይሆንም።

፭/ በአቅርቦቱ ላይ የተጣለው ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን የሚሰላው ለአቅርቦቱ ከተወሰነው አንድ የገንዘብ መጠን በመቶኛ ወይም በክፍልፋይ የሆነ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ በክፍያ፣ በዕቃ እና በአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን ላይ እንደሁኔታው ሌላ ጭማሪ ወይም ቅናሽ ማድረግን የሚፈቅድ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

## ፴፯. በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በሚከናወን አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም ላይ የሚደረግ ለውጥ

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ የአቅርቦቱ ዋጋ የሚወሰነው በሚከተለው ሁኔታ፣ ይሆናል፦

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፩(፬) በተመለከተው በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚከናወን አቅርቦት፣ የዕቃ አቅርቦት የተፈጸመው ወይም አገልግሎት የተሰጠው የሚከተሉት ከመጀመራቸው በፊት ወይም በሚጠናቀቁበት ጊዜ ወይም ከተጠናቀቁ በኋላ ከሆነ፦

(i) በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተጣለበት ቀን፣ ወይም

(ii) በአቅርቦቱ ላይ ተጥሎ የነበረው የተጨማሪ እሴት ታክስ የተነሳበት ቀን፣

ለ) ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የቀረበበት ቀን በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ ቀን በኋላ ከሆነ፡፡

4/ Sub-Article (3) of this Article shall not apply if the fee, charge, or other amount has been altered in any Proclamation, Regulation, or Directive to take account of any imposition, increase, decrease, or withdrawal of VAT.

5/ Nothing in Sub-Article (3) of this Article shall be construed so as to permit any further increase or require any further decrease, as the case may be, in a fee, charge, or other amount if the fee, charge, or other amount is calculated as a percentage or fraction of another amount that represents the consideration for a taxable supply.

## 37 .Application of a Change in VAT Treatment to Periodic Supplies

1/ Sub-Article (2) of this Article applies where the following conditions are satisfied:

a) goods are provided or services performed under a periodic supply referred to in Article 21(4) of the Proclamation during a period beginning before and ending on, or after, the date on which:

(i) A change in the VAT rate applicable to the supply becomes effective;

(ii) VAT is imposed in respect of the supply; or

b) The time of supply of the goods or services is on or after the date referred to in Paragraph (a) of this Sub-Article.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሁኔታዎች የተሟሉ በሚሆንበት ጊዜ፡-

ሀ) አዲስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢጣል፤ ታክሱ ከመጣሉ በፊት ላለው አቅርቦት አዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም፤ ወይም

ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢነሳ፤ ታክሱ ከመነሳቱ በፊት ያለው አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዳልተነሳ ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልበታል።

፴፰. **<u>በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የሚደረግ ለውጥ በሌሎች ሁኔታዎች የሚኖረው ተፈፃሚነት</u>**

፩/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተፈፃሚ ይሆናል፦

ሀ) ከማይንቀሳቀስ ንብረት በስተቀር አቅራቢው ከሚከተለው ጊዜ በፊት ያቀረባቸው ዕቃዎች ሲሆኑ፡-

(i) በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተጣለበት ቀን በፊት፤ ወይም

(ii) በአቅርቦቱ ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተነሳበት ቀን በፊት፤

ለ/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የዕቃው አቅርቦት የተፈፀመው በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ሲሆን፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) (i) በተመለከተው መሠረት ከአዲሱ ታክስ ጋር በተያያዘ አቅርቦቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፤ ወይም

2/ Where the conditions in Sub-Article (1) of this Article are satisfied, the value of the supply is:

a) If a new VAT is imposed; the new VAT will not be payable on supplies made before the tax was imposed; or

b) For the withdrawal of VAT, the first part is subject to VAT as if VAT had not been withdrawn.

38 .**<u>Application of a Change in VAT Treatment in Other Cases</u>**

1/ Sub-Article (2) of this Article shall apply where the following conditions are satisfied:

a) goods, other than immovable property, are provided by a supplier before the date on which:

(i) A change in the VAT rate applicable to the supply becomes effective;

(ii) VAT is withdrawn in respect of the supply; and

b) The time of the supply of the goods under Article 21 of the Proclamation is on, or after, the date referred to in Paragraph (a) of this Sub-Article.

2/ Where the conditions in Sub-Article (1) of this Article are satisfied:

a) The supply is deemed to be exempt from value added tax in respect of the new tax in accordance with sub-article (1) (a) (i) of this article; or

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) (ii) በተመለከተው መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚነሳበት ጊዜ አቅርቦቱ ታክሱ እንዳልተነሳለት ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፤

፫/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተፈፃሚ ይሆናል፦

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተመለከተው መሠረት በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በሚከናወን አቅርቦት ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ አገልግሎት የተሰጠ ወይም የዕቃ አቅርቦት የተከናወነ በሚሆንበት ጊዜ፡-

(i) በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተጣለበት ቀን፤ ወይም

(ii) በአቅርቦቱ ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተነሳበት ቀን፤

ለ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የእቃው አቅርቦት እና አገልግሎት የመስጠቱ ተግባር የተከናወነበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ ቀን በኋላ ከሆነ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ፤

ሀ) የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዲስ መልክ የተጣለ ሲሆን፤ አቅርቦቱ ተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፤

ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ የተነሳ እንደሆነ፤ ታክሱ እንዳልተነሳ ተቆጥሮ ግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፤

b) for the withdrawal of VAT referred to in Sub-Article (1) (a) (ii) of this Article, the supply shall be treated as being subject to VAT as if VAT had not been withdrawn.

3/ Sub-Article (4) of this Article applies where the following conditions are satisfied:

a) Services are performed or goods, other than immovable property, are provided in respect of a periodic supply referred to in Article 21 Sub-Article (4) of the Proclamation during a period beginning and ending before:

(i) A change in the VAT rate applicable to the supply becomes effective;

(ii) VAT is withdrawn in respect of the supply; and

b) The time of the supply of the goods or services under Article 21 of the Proclamation is on or after the date referred to in Paragraph (a) of this Sub-Article.

4/ Where the conditions in Sub-Article (3) of this Article are satisfied:

a) When the value-added tax has been introduced as a new; the supply is considered to be exempt from value-added tax;

b) For the withdrawal of VAT, the supply is treated as being subject to VAT as if VAT had not been withdrawn.

፭/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የዚህ አንቀስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተግባራዊ ይሆናል፦

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተመለከተው መሠረት፣ በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በሚከናወን አቅርቦት ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ አገልግሎት የተሰጠ ወይም የዕቃ አቅርቦት የተከናወነ በሚሆንበት ጊዜ፣

(i) በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተጣለበት ቀን፣ ወይም

(ii) በአቅርቦቱ ላይ ተጥሎ የነበረ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተነሳበት ቀን፣

ለ) የዕቃ እና አገልግሎት አቅርቦት ተፈፅሟል የሚባለው በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ ቀን በኋላ ነው፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተመለከቱት ሁኔታዎች የተሟሉ በሚሆንበት ጊዜ፣ የአቅርቦቱ ዋጋ የሚወሰነው በሚከተለው ሁኔታ ነው፦

ሀ) አዲስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢጣል፣ አዲሱ ታክስ ከመጣሉ በፊት የነበረው ግብይት አዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም፣ ወይም

ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢነሳ፣ ታክሱ ከመነሳቱ በፊት የነበረው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዳልተነሳ ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልበታል።

፯/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፫) እና (፭) አፈፃፀም፣ ዕቃን በሚመለከት የአቅርቦት ተቀባዩ ዕቃውን በተረከበ ጊዜ እንዲሁም አቅርቦቱ የተፈጸመው በኪራይ ውል በሚሆንበት ጊዜ ዕቃው በአቅርቦቱ ተቀባይ ይዞታ ስር በዋለበት ጊዜ አቅራቢው አቅርቦቱን እንደፈፀመ ይቆጠራል።

5/ Sub-Article (6) of this Article applies where the following conditions are satisfied:

a) Services are performed or goods, other than immovable property, are provided in respect of a periodic supply referred to in Article 21 Sub-Article (4) of the Proclamation during a period beginning before and ending on, or after, the date on which:

(i) VAT is imposed in respect of the supply; or

(ii) VAT is withdrawn in respect of the supply, and

b) The time of supply of the goods or services is on or after the date referred to in Paragraph (a) of this Sub-Article.

6/ When the conditions set forth in Sub-Article (5) of this Article are met, the value of the supply shall be determined as follows:

a) If a new VAT is imposed; the transaction that took place before the new tax was imposed may not be subject to the new VAT; or

b) If VAT is withdrawn, the transaction that occurred before the tax was withdrawn shall be considered the VAT have not to been withdrawn and the VAT shall be payable.

7/ For the purposes of Sub-Articles (1), (3), and (5) of this Article, goods shall be treated as provided by the supplier at the time that the goods are delivered to the recipient and goods supplied under a rental agreement shall be treated as provided to the recipient when the recipient takes possession or occupation of the goods.

## ክፍል ዘጠኝ

## የውጭ አቅራቢዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር

### ፴፱. የዚህ የደንቡ ክፍል ተፈፃሚነት

፩/ ይህ የደንቡ ክፍል ተፈፃሚ የሚሆነው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከተለው የገንዘብ መጠን በላይ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ባላቸው የውጭ አገር አቅራቢዎች ላይ ነው።

፪/ ለዚህ የደንቡ ክፍል አፈጻጸም "የውጭ አቅራቢ" ማለት፦

ሀ) የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተፈፃሚ የሚሆንበት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝ እቃ አቅራቢ፣

ለ) የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደልተራ (ሐ) ተፈፃሚ የሚሆንበት ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት አቅራቢ፣ ወይም

ሐ) የአዋጅ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና አንቀጽ ፳፭ ተፈፃሚ የሚሆንበት የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያ መድረክ አንቀሳቃሽ፣ ነው።

### ፵. በኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቅርቦትን ስለማከናወን

፩/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ በተመዘገበ ወኪል በኩል ካልሆነ በስተቀር የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትን ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ሰዎች የሚያቀርብ ነዋሪ ያልሆነ እና ለታክሱ ያልተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን ከሆነ ለታክሱ መመዝገብ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አቅርቦት ከነጋዴ ወደ ነጋዴ ግብይት የተፈፀመ ከሆነ፣ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ተፈፃሚ ይሆናል።

## PART NINE

## VAT ADMINISTRATION FOR FOREIGN SUPPLIERS

### 39. Application of this Part of these Regulations

1/ This Part shall apply to a foreign supplier who makes taxable supplies in excess of the registration threshold.

2/ In this Part, "foreign supplier" means:

a) a supplier of electronically ordered goods to which Article 23 Sub-Article (2) of the Proclamation applies:

b) a supplier of remote services to which Article 24 Sub-Article (2) paragraph (c) of the Proclamation applies; or

c) an operator of an electronic distribution platform to which Articles 23 Sub-Article (3) and Article 25 of the Proclamation apply.

### 40. Supply of Goods and Services by Electronic Means

1/ A non-resident and unregistered person who supplies telecommunications services or goods and services electronically to individuals in Ethiopia, unless through a VAT-registered agent, must register for VAT.

2/ If the supply mentioned in Sub-Article (1) of this Article is conducted as a merchant-to-merchant transaction, the provisions of Article 6 of the Proclamation shall apply.

፫/ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርቡ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች፣ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን የሚጨምር ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡ -

ሀ) ማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ጨዋታ፤ የኤሌክትሮኒክ ውርርድ፤

ለ) በበይነመረብ ላይ የተመሰረተ የጨረታ አገልግሎት መስጫ አቅርቦት፤

ሐ) የማንኛውም ዲጂታል ይዘት ያለው መጽሐፍ ወይም ሕትመትን ጨምሮ የኤሌክትሮኒክ መጽሐፍ አቅርቦት፤

መ) በተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ የሚጫኑ ዲጂታል ይዘት ያላቸው መተግበሪያዎች፣ ኢ-መጽሐፍት እና ፊልሞች፣

ሠ) በደንበኝነት ምዝገባ ላይ የተመሰረተ ሚዲያ ዜና፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች እና ሙዚቃዎች፣ ፖድካስቶች፣ ብሎግ፣ ጆርናል፣ ወቅታዊ ሕትመት፣ የማህበራዊ ትስስር አገልግሎት፣ ድር ጣቢያ፣ እና የድር መተግበሪያን ማቅረብ፤

ረ) የሶፍትዌር ፕሮግራሞችን፣ ድራይቨር፣ የድር ጣቢያ እና ፋየርዎሎች፤

ሰ) የኤሌክትሮኒክስ መረጃ አስተዳደር የድር ጣቢያ ማስተናገጃ፣ የመስመር ላይ ውሂብ ማከማቻ፣ የፋይል መጋራት እና ክላውድ ማከማቻ አገልግሎቶች፤

ሸ) የሙዚቃ አቅርቦት (የድምጽ ቅንጥብ፣ ስርጭት፣ የቀጥታ ስርጭት፣ የስልክ ጥሪ ድምፅ፣ ዘፈን፣

ቀ) የሰርች ኢንጅን አገልግሎቶችን ጨምሮ አውቶሜትድ የእርዳታ ዴስክ አገልግሎቶች አቅርቦት፤

በ) ለቀጥታ ዝግጅቶች፣ ቲያትሮች፣ ምግብ ቤቶች ወዘተ የሚውሉ ትኬቶች በኢንተርኔት በኩል መሸጥ፤

3/ Taxable supplies provided by electronic means include electronic services, such as:

a) Any electronic game; electronic betting;

b) Provision of internet-based bidding services;

c) The provision of electronic books, including books or publications, or any digital content;

d) Applications, e-books, and movies containing digital content that can be installed on a mobile phone;

e) Subscription-based media services including news, magazines, newspapers, television programs, music, podcasts, blogs, journals, periodicals, social networking services, websites, and web applications;

f) Software programs, drivers, websites, and firewalls;

g) Electronic information management, including website hosting, online data storage, file sharing, and cloud storage services;

h) Provision of music (audio clips, broadcasts, live streams, ringtones, songs);

i) Provision of search engine and automated help desk services, including related search engine services;

j) Sale of tickets for live events, theatres, restaurants, etc., over the Internet;

ተ) በማንኛውም የድምጽ ቪዥዋል ወይም ዲጂታል ሚዲያ ላይ ለማዳመጥ፣ ለማየት ወይም ለመጫወት የሚያስችል የዲጂታል ይዘት አቅርቦት፤

ቸ) የገንዘብ ሚኒስቴር የሚወስናቸው ማናቸውም ሌላ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርቡ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች፡፡

፵፩. **የውጭ አቅራቢን ስለመመዝገብ**

፩/ ይህ የደንቡ ክፍል ተፈፃሚ የሚሆንበት የውጭ አቅራቢ ለዚህ ዓይነት አቅራቢዎች በታክሱ ባለሥልጣን የጸደቀውን የምዝገባ ቅጽ በመጠቀም በኦንላይን የምዝገባ ዘዴ ለመመዝገብ ማመልከት አለበት።

፪/ የውጭ አቅራቢዎች የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፤

ሀ) የንግድ ስሙን ጨምሮ የውጭ አቅራቢውን ስም፤

ለ) የውጭ አቅራቢውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ ፋክስ እና የሚገኝበትን የኤሌክትሮኒክ ዝርዝር፤

ሐ) የውጭ አቅራቢው በኢትዮጵያ የሚኖርበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ግዴታ የሚወጣለትን ሰው ሰም፤ አድራሻ፤ የስልክ ቁጥር፤ ፋክስ እና የሚገኝበትን የኤሌክትሮኒክ ዝርዝር፤

መ) የውጭ አቅራቢው ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውንበት ዌብሳይት ወይም ዩኒፎርም ሪሶርስ ሎኬተር(ዩ አር ኤል)፤

ሠ) የውጭ አቅራቢው ነዋሪ በሆነበት አገር የተሰጠው ብሄራዊ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፤

ረ) የውጭ አቅራቢው የንግድ ስራ በተመዘገበበት ወይም በተቋቋመበት አገር የተሰጠው የምስክር ወረቀት፤ እና

k) Provision of digital content for listening, viewing, or playing on any audio-visual or digital media;

l) Any other taxable supplies made by electronic means as determined by the Ministry of Finance.

41. **Registration of Foreign Suppliers**

1/ A foreign supplier to whom this Part applies shall apply for registration through an online lodgement of the registration form approved by the Tax Authority for such suppliers.

2/ The application form for foreign suppliers shall require the following information:

a) the name of the foreign supplier including the trading name;

b) the address, and phone, facsimile, and electronic contact details of the foreign supplier;

c) the name, and phone, facsimile, and electronic contact details of the person responsible for compliance with the foreign supplier's Ethiopian VAT obligations;

d) the website or uniform resource locator (URL) of the foreign supplier through which the taxable activity of the supplier is carried on;

e) the national tax identification number issued to the foreign supplier in the supplier's country of residence;

f) the certificate of incorporation or registration issued to the foreign supplier in the country where the supplier's business is registered or incorporated; and

ሰ) የታክሱ ባለስልጣን የሚጠይቀው ሌላ መረጃ፣

፫/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የውጭ አቅራቢው በምዝገባ ማመልከቻው የሰጣቸውን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።

፬/ የታክሱ ባለሥልጣን የውጭ አቅራቢውን ከመዘገበ በኋላ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል የሚያስችለውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር መስጠት አለበት።

፭/ ታክስ የሚከፈልባቸውን አቅርቦቶች ማቅረብ ያቋረጠ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ መሠረት ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።

**፵፪. <u>የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች</u>**

፩/ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ ለሚያቀርባቸው ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የታክስ ደረሰኝ መስጠት የለበትም፣ ሆኖም የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፦

ሀ) ለኢንቮይሱ ወይም ለደረሰኙ በተለይ የተሰጠ ቁጥር፣

ለ) የውጭ አቅራቢውን ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣

ሐ) የአቅርቦቱን ተቀባይ ስም እና አድራሻ፣

መ) አቅርቦቱ የተፈጸመበትን ቀን፣

ሠ) የዕቃዎቹን እና ከሩቅ የተሰጡትን አቅርቦቶች መግለጫ፣ እና

ረ) ለአቅርቦቱ የተከፈለውን ዋጋ እና የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ።

g) any other information as the Tax Authority may require.

3/ The Tax Authority may require an applicant under Sub-Article (1) of this Article to lodge additional documents as may be necessary to substantiate the information provided in the registration application.

4/ Upon registration, the Tax Authority shall issue the foreign supplier with a TIN and VAT registration number for the purposes of filing returns and paying VAT.

5/ A registered foreign supplier who ceases to make taxable supplies shall notify the Tax Authority in accordance with Article 16 of the Proclamation.

**42. <u>VAT Documentation for Registered Foreign Suppliers</u>**

1/ A registered foreign supplier shall not issue a tax invoice in relation to taxable supplies made but shall issue an electronic invoice or receipt specifying the following:

a) the individual serial number of the invoice or receipt;

b) the name, address, TIN, and VAT registration number of the foreign supplier;

c) the name and address of the recipient of the supply;

d) the date of the supply;

e) a description of the goods or remote services supplied; and

f) the consideration for the supply and the VAT charged.

፪/ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶችን በውጭ አገር ሊይዝ የሚችል ሲሆን፣ በታክሱ ባለስልጣን በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ በሚወሰን ቀን እነዚህን ሰነዶች እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ አለበት።

**፵፫. <u>በተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ከሂሳብ ጊዜው ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ወይም ከዚያ በፊት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት።

፪/ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የታክስ ማስታወቂያውን በየሶስት ወሩ ማቅረብ እንዲፈቀድለት ሊጠይቅ ይችላል። የታክሱ ባለስልጣን የውጭ አቅራቢው በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሰረት ግዴታውን የሚወጣ መሆኑን ካመነበት በጥያቄው መሠረት ሊፈቅድ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ካገኘ የውጭ አቅራቢው የሂሳብ ጊዜ ሶስት ወር ይሆናል።

፬/ የታክስ ማስታወቂያውን በየሦስት ወሩ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት የውጭ አቅራቢ የታክስ ማስታወቂያውን በወቅቱ የማያቀርብ እና የተጨማሪ እሴት ታክሱን በወቅቱ የማይከፍል ከሆነ የታክሱ ባለስልጣን በየሦስት ወሩ የታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል።

፭/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ሶስት ወር" ማለት በግሪጎሪያን ቀን መቁጠሪያ ውስጥ ባለው በሦስተኛው፣ በስድስተኛው፣ በዘጠነኛውና በአስራ ሁለተኛው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ የሦስት ወር ጊዜ ነው።

2) A registered foreign supplier may maintain VAT documentation outside Ethiopia and shall make the documentation available to the Tax Authority on request by notice in writing and by the date specified in the notice.

**43. <u>Filing of VAT Returns by Registered Foreign Supplier</u>**

1/ Subject to Sub-Article (2), a registered foreign supplier shall file a VAT return electronically for each accounting period on or before the last day of the month following the end of the period.

2/ A registered foreign supplier may apply to the Tax Authority for permission to file VAT returns quarterly and the Tax Authority shall grant the application if the foreign supplier is reasonably expected to comply with their VAT obligations under the Proclamation and these Regulations.

3/ Where an application under Sub-Article (2) of this Article has been granted, the accounting period of the registered foreign supplier shall be the quarter.

4/ Where a foreign supplier who has been granted permission to file quarterly VAT returns fails to file or pay VAT by the due date, the Tax Authority may withdraw the permission to file quarterly.

5/ In this Article, "quarter" means the period of three months ending on the last day of the third, sixth, ninth, and twelfth months of the calendar year.

**፵፬ በተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ**

፩/ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ በሂሳብ ጊዜው ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ ባለበት ጊዜ መክፈል አለበት።

፪/ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈለው የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው የኤሌክትሮኒክ ዘዴ መሆን አለበት።

፫/ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የታክሱ ባለሥልጣን በሚፈቅደው መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክሱን በአሜሪካ ዶላር፣ በዩሮ፣ በእንግሊዝ ፓውንድ ወይም በሌላ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያፀድቀው የውጭ አገር ገንዘብ ሊከፍል ይችላል።

**ክፍል አስር**

**ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው አቅርቦቶች**

**፵፭. ወደውጭ ስለሚላኩ ዕቃዎች**

በአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፩ እና ፪ መሠረት ወደውጭ የሚላኩ ዕቃዎች እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ እንዲሆንላቸው ማድረግ የሚቻለው የታክሱ ባለሥልጣን በሚያዘው መሠረት ላኪው በወጪ ዕቃዎች ወደብ ዕቃዎቹን እና የጽሑፍ ማስረጃዎችን ለይቶ ሲያቀርብ ይሆናል።

**፵፮. ለላኪ ዕቃዎችን ስለማቅረብ**

፩/ በአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፬ ፊደል ተራ (መ) "ዕቃዎችን ወደውጪ መላክ" ለተሰጠው ትርጉም አፈፃፀም የተመዘገበ ሰው ለውጭ ገበያ ለሚያቀርብ ለሌላ የተመዘገበ ሰው (ላኪ) የሚያቀርባቸው ዕቃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ለውጭ ገበያ የተላኩ እንደሆነ ይቆጠራል፦

ሀ) የዕቃውን ዓይነት እና አግባብነት እስካለው ድረስ የላኪውን መደበኛ አሰራር እንዲሁም ምክንያታዊ የሆነውን የጉዳዩን አፈፃፀም ከግምት ውስጥ በማስገባት ላኪው እነዚህን ዕቃዎች እንደተረከበ ወዲያውኑ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ከሆነ፣

**44. Payment of VAT by a Registered Foreign Supplier**

1/ A registered foreign supplier shall pay the VAT due for an accounting period by the due date for the VAT return for the period.

2/ VAT shall be paid electronically in accordance with a Directive issued by the Ministry of Revenue.

3/ A registered foreign supplier may, with the permission of the Tax Authority, report and pay VAT in United States dollars, Euros, British Pounds, or other foreign currency as approved by the Ministry of Revenue.

**PART TEN**

**ZERO-RATED SUPPLIES**

**45. Export of Goods**

For an export of goods or related services to qualify for zero-rating under Part 1 and 2 of Schedule 1 of the Proclamation, the exporter shall identify the goods and present documentary proof as required by the Tax Authority at the port of exit.

**46. Supply of Goods to Exporter**

1/ For the purposes of paragraph (d) of the definition of "export of goods" in Part 4 of Schedule 1 of the Proclamation, a supply of goods made by a registered person to another registered person (exporter) who will export the goods is treated as an export of goods if all of the following conditions are met:

a) the exporter exports the goods as soon after the goods are delivered to the exporter as is reasonable having regard to the facts of the situation, including the type of goods involved and, where applicable, the normal business practice of the exporter;

ለ) ላኪው እነዚህን ዕቃዎች የተረከበው ለፍጆታ፣ ለመጠቀሚያ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ለገበያ ለማቅረብ ካልሆነ፣

ሐ) የዕቃዎቹ ርክክብ ከተፈፀመ በኋላ ዕቃዎቹን ለማጓጓዝ አስፈላጊ ካልሆነ ወይም የማጓጓዙ አካል ካልሆነ በስተቀር ዕቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደገና ለመሰራት፣ ለመለወጥ ወይም ተሻሽለው ለመሰራት የማይውሉ ከሆነ፣ እና

መ) ላኪው ዕቃዎቹ ለውጭ ገበያ የተላኩ መሆኑን የሚያስረዱ የታክስ ባለሥልጣኑን የሚያሳምኑ ማስረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም፦

ሀ) ላኪው ዕቃዎችን ለመላክ ያቀደ እና ዕቃዎቹን የሚልክ መሆን አለበት፣

ለ) ዕቃዎችን ወደውጭ ለመላክ ላቀደ ላኪ ዕቃዎችን ለሚያቀርብ ሰው የሚፈፀም አቅርቦት ለውጭ ገበያ የተላከ እንደሆነ አይቆጠርም፣

ሐ) እንደገና መስራት፣ መለወጥ ወይም አሻሽሎ መስራት ከተፈጥሮዓዊ እድገት ውጪ ዝግጅትን፣ አያያዝን ወይም ሌላ በእቃው ላይ አካላዊ ወይም ኬሚካላዊ ለውጥ ማስከተልን ይጨምራል፣ ሆኖም ቆጠራን፣ ማቀዝቀዝን፣ በመጋዘን ማከማቸትን፣ለውጭ ገበያ በሚላክበት አኳኋን ማሸግን፣ መልሶ ማሸግን፣ የኤክስፖርት ምልክት ማድረግን፣ ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ዓይነት በሳጥን ማሸግን፣ መጫንን ወይም ከአንዱ ወደሌላ ማስተላለፍን፣ እና

መ) የታክሱን ባለሥልጣን በሚያሳምን አኳኋን ዕቃው ለውጭ ገበያ ለመቅረቡ በቂ ማስረጃ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በታክሱ ባለሥልጣን ተቀባይነት ባለው ቅርፅ ከዕቃው ተቀባይ እንደ የኤክስፖርት ሠርተፊኬት ያለ ማስረጃ ሲቀርብ ነው።

b) the exporter has not acquired the goods for consumption, use, or supply in Ethiopia before exportation;

c) the goods are not to be further processed, transformed, or altered in Ethiopia, except to the extent reasonably necessary or incidental to transportation of the goods, after delivery and before its exportation; and

d) the supplier shall maintain evidence satisfactory to the Tax Authority of exportation of the goods by the exporter.

2/ For purposes of Sub-Article (1):

a) the exporter must intend to export the goods and must in fact export the goods;

b) a supply to a person who intends to sell the goods to an exporter who will export the goods shall not be treated as a supply to an exporter;

c) processing, transformation, or alteration includes preparation, handling or other activity that causes a physical or chemical change in the property, other than natural growth, but generally does not include services such as stocktaking, refrigeration, warehousing, export packing or repacking, export labelling, export crating, loading, or uploading; and

d) evidence of exportation can be satisfied with documents satisfactory to the Tax Authority, such as an export certificate from the recipient of the goods in a form acceptable to the Authority.

፫/ በዚህ አንቀጽ "ዕቃ" የተፈጥሮ ሀብት የሚጨምር ሲሆን፣ የአልኮል እና የትምባሆ ውጤቶችን አይጨምርም።

**፵፯. <u>አገልግሎትን ወደ ውጭ ስለመላክ</u>**

ለአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፪ አንቀጽ ፩ (ሀ) አፈፃፀም የሚከተሉት ከኢትዮጵያ ውጪ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም ለፍጆታ የሚውሉ አገልግሎቶች እንደሆኑ ይቆጠራል፦

ሀ) አገልግሎቱ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ከሆነ፣

ለ) ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ የተሰጠን የአገልግሎት አቅርቦት ሳይጨምር አገልግሎቱ የተሰጠው አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ነዋሪ ለሆነ ሰው ከሆነ፦

(i) በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ከሆነ፣

(ii) አገልግሎቱ ከተሰጠ በኋላ የሚንቀሳቀሰው ንብረት ከኢትዮጵያ ውጪ የተላከ ካልሆነ በስተቀር አገልግሎቱ የተሰጠው አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ ከሆነ፣

(iii) አገልግሎቱ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ ከማካሄድ መቆጠብን የሚመለከት ከሆነ፣

(iv) ሌላ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ማካሄዱን መቀበልን የሚመለከት ከሆነ፡፡

ሐ) የሚሰጡት አገልግሎቶች፦

(i) የፈጠራ መብትን ከኢትዮጵያ ውጪ ለመጠቀም ማስመዝገብ፣ መከታተል፣መስጠት፣ ማደስ፣ ማዘዋወር፣ መብት ማስተለለፍ፣ ፈቃድ ማውጣት ወይም ማስፈጸም፣

(ii) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሐ) (i) የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ተዛማጅ አገልግሎቶች፣ ወይም

3/ In this Article, "goods" includes natural resources, but does not include alcohol or tobacco products.

**47. <u>Export of Services</u>**

For the purposes of Article 1(a) of Part 2 of Schedule 1 of the Proclamation, the following are treated as services for use or consumption outside Ethiopia:

a) the services are supplied directly in connection with immovable property located outside Ethiopia;

b) the services are supplied to a non-resident person who is outside Ethiopia at the time the services are supplied, other than a supply of services:

(i) directly in connection with immovable property situated in Ethiopia;

(ii) directly in connection with movable property situated in Ethiopia at the time the services are supplied unless the movable property is exported from Ethiopia subsequent to the supply of services;

(iii) comprising the refraining from undertaking any taxable activity in Ethiopia; or

(iv) comprising the tolerating of another person undertaking any taxable activity in Ethiopia.

c) the services are:

(i) the filing, prosecution, granting, maintenance, transfer, assignment, licensing, or enforcement of intellectual property rights for use outside Ethiopia;

(ii) incidental services necessary for the supply of services referred to in Sub-paragraph (i) of this Paragraph; or

(iii) ከኢትዮጵያ ውጪ የፈጠራ መብቶችን በሙሉ ወይም በከፊል ለመጠቀም ማናቸውም ሰው አንድን ነገር ከመከታተል ወይም ከማድረግ ለመቆጠብ የሚገባው ግዴታ፡፡

**፵፰. አለም ዓቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት**

፩/ በአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፬ ፊደል ተራ "መ" ለተተረጎመው "አለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት" አፈፃፀም የሚከተሉት የአለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ተደርገው ይቆጠራሉ፦

ሀ) አውሮፕላኑ በኪራይ ወይም በቻርተር ውሉ ዘመን በተላከበት የውጭ አገር ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ በኪራይ ወይም በቻርተር ውል መሠረት የቀረበ አውሮፕላን፤

ለ) ለውጭ አገር አውሮፕላን የተሰጠ የጥገና፣ የዕድሳት፣ የፅዳት ወይም የጠቅላላ ዕድሳት አገልግሎት፤

ሐ) በወኪል ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው በቀጥታ የሚሰጥ የሚከተሉትን የሚጨምር አገልግሎት፡-

(i) ወደውጭ ሀገር ለሚሄድ አውሮፕላን ኢትዮጵያ ውስጥ ባለበት ጊዜ የሚሰጥ የማስተናገድ፣ ወደመቆሚያ ወይም ከመቆሚያ በመውጣት ሂደት ማገዝ፣ የሳልቬጅ ወይም የመጎተት አገልግሎት፣ ወይም

(ii) ለውጭ ሀገር አውሮፕላን ከስራ እንቅስቃሴ ወይም አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚሰጥ አገልግሎት፤

(iii) the acceptance by any person of an obligation to refrain from, pursuing, or exercising, in whole or part, intellectual property rights for use outside Ethiopia.

**48. International Transport Services**

1/ The following are treated as a supply of international transport services for the purposes of Paragraph (d) of the definition of "international transport services" in Part 4 of Schedule 1:

a) a supply of an aircraft under a rental or charter agreement, where the aircraft is to be used exclusively in an export country for the period of the lease or charter;

b) a supply of services directly in respect of the repair, maintenance, cleaning, or reconditioning of a foreign-going aircraft;

c) a supply of services directly to a non-resident person not being a registered person, otherwise than through an agent or other person:

(i) comprising the handling, pilotage, salvage, or towage of any foreign-going aircraft while situated in Ethiopia; or

(ii) provided in connection with the operation or management of any foreign-going aircraft;

መ) በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው የሚከተሉትን በማመቻቸት ረገድ የሚሰጥ አገልግሎት፦

(i) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) (ለ) ወይም (ሐ) ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን አገልግሎቶች ማቅረብ፤ ወይም

(ii) ተጓዳኝ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ እቃዎችን ማጓጓዝ፤

ሠ) ነዋሪ ያልሆነ ያልተመዘገበ ሰው ለሚሰጠው የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የጥገና፤ የእድሳት፤ የጽዳት ወይም የጠቅላላ ዕድሳት አገልግሎት አቅርቦት፤ እና

ረ) በጉዞ ወኪል አማካኝነት የአለም ዓቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን ማመቻቸት፡፡

፪/ የጉዞ ወኪል ጥቅል የቱሪዝም አገልግሎትን የሚያካትት የጉዞ ጥቅል እና አለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉት ሲሟሉ የአዋጁ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ተፈፃሚ ይሆናሉ፦

ሀ) የአለም ዓቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት እና የጉዞ ወኪሉ አለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎትን በማመቻቸት ረገድ የሚሰጠው አገልግሎት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግባቸው ከሆነ፤ እና

ለ) ጥቅል የቱሪዝም አቅርቦቱ እና የጉዞ ወኪሉ ጥቅል የቱሪዝም አገልግሎት በማመቻቸት ረገድ የሚሰጠው አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸው ከሆነ፡፡

d) a supply of services to a non-resident person who is not a registered person comprising the arranging for the person of:

(i) a supply of services to which Sub-Article (2)(b) or (c) of this Article applies; or

(ii) the transport of goods, including ancillary transport services, within Ethiopia;

e) a supply of services comprising the repair, maintenance, cleaning, or reconditioning of a railway train operated by a non-resident person who is not a registered person; and

f) the arranging of a supply of international transport services by a travel agent.

2/ Article 20 Sub-Article (5) and (6) of the Proclamation shall apply where a travel agent arranges a travel package for a client that includes an inbound tourism product or products, and international transport services on the basis that:

a) the supply of the international transport services and services of the travel agent in arranging the international transport services are zero-rated supplies; and

b) the supply of the inbound tourism product or products, and the services of the travel agent in arranging the inbound tourism product or products, are taxable supplies subject to VAT at the rate specified in Article 8 Sub-Article (2)(b) of the Proclamation.

፫/ በዚህ አንቀጽ “ወደውጭ አገር የሚጓዝ አውሮፕላን” ማለት መንገደኞችን ወይም ዕቃ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በኢትዮጵያ ከሚገኝ የአውሮፕላን ማረፊያ በውጭ አገር ወደሚገኝ አውሮፕላን ማረፊያ ወይም በውጭ አገር በሚገኙ አውሮፕላን ማረፊያ ከአንዱ ወደሌላው የሚያጓጉዝ አውሮፕላን ነው።

**፵፱. <u>የፋይናንስ አገልግሎትን ወደ ውጭ ስለመላክ</u>**

የሚከተሉት ለወጭ የሚቀርቡ የፋይናን አገልግሎቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግላቸዋል፡-

፩/ ወደውጭ ከሚላኩ እቃዎች ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎቶች፤

፪/ ለውጭ ገበያ የሚላኩ እቃዎችን ወጪ ለመሸፈን ነዋሪ ላልሆነ እና ላልተመዘገበ ሰው ከሚሰጥ ብድር ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ተጓዳኝ የፋይናንስ አገልግሎቶች፤ እና

፫/ በአዋጁ የዚህ አይነቱ አቅርቦት ኤክስፖርት የማይባል ካልሆነ በስተቀር አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ለነበረ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ባንክ የተሰጠ የባንክ አገልግሎት፡፡

**፶. <u>ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ በስራ ላይ እንዳለ ድርጅት ስለማስተላለፍ</u>**

፩/ ይህ አንቀጽ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ የስራ እንቅስቃሴ ከፊል በስራ ላይ እንዳለ ድርጅት ሲተላለፍ ዜሮ የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ እንድሚደረግለት ለሚደነግገው የአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፫ አንቀፅ ፩(ሀ) አፈጻጸም የሚያገለግል ነው።

፪/ በስራ ላይ ያለ ድርጅት ወይም የዚሁ ድርጅት ከፊል ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በማስተላለፍ ሂደት የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት ተፈጽሟል የሚባለው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነበት ጊዜ ነው።

3/ In this Article, “foreign going aircraft” means an aircraft engaged in the transportation for reward of passengers or goods wholly or mainly on flights between airports in Ethiopia and airports in export countries or between airports in export countries.

**49. <u>Export of Financial Services</u>**

The following are zero-rated exports of financial services:

1/ financial services supplied in connection with an export of goods;

2/ financial intermediation services supplied in connection with a loan to an unregistered, non-resident person to finance the export of goods; and

3/ banking services supplied by an Ethiopian bank to a non-resident who is outside Ethiopia at the time services are supplied unless the services are excluded from being an export under the Proclamation.

**50. <u>Transfer of a Taxable Activity as a Going Concern</u>**

1/ This Regulation shall apply for the purposes of Article 1(a) of Part 3 of Schedule 1 of the Proclamation, which provides that the transfer of a taxable activity or part of a taxable activity as a going concern is a zero-rated supply.

2/ A supply of goods or services as part of the transfer of a taxable activity, or part of a taxable activity, as a going concern shall occur at the time of the transfer.

፫/ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ እንቅስቃሴ ክፊል በስራ ላይ ያለ ነው የሚባለው የማስተላለፉ ተግባር ከተፈፀመ በኋላ የስራ እንቅስቃሴው ያለማቋረጥ የሚከናወን ወይም ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው። ስራውን ያቋረጠ ወይም ወደፊት ሊሰራ ይችላል የሚባል ድርጅት በስራ ላይ ያለ ነው ሊባል አይችልም።

፬/ የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ የስራ እንቅስቃሴ ክፊል ትርፋማ ባይሆንም ወይም የተላለፈው ለኪሳራ አጣሪ፤ ለተቀባይ፤ በኪሳራ ሂደት ለተሰየመ ባለአደራ ወይም የተመዘገበው ሰው ኪሳራ በመጣራት ላይ ባለበት ሂደት ለተሰየመ ሌላ ሰው ቢሆንም በስራ ላይ እንዳለ ይቆጠራል።

፭/ በተመዘገበ ሰው በስራ ላይ እንዳለ ድርጅት የተላለፈ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ የስራ እንቅስቃሴ ክፊል ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግለት ነባር ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴን የማስተላለፉ ተግባር እንደገና በማደራጀት ሂደትን የመሳሰለ ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ የህግ ሰውነት ወይም ቅርጽ የመለወጥ ሲሆን ነው።

፮/ የተላለፈለት ሰው እና አስተላላፊው ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ከሆኑ ወይም የተላለፈለት ሰው ታክስ በሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ላይ አስቀድሞ ጥቅም የነበረው ከሆነ የታክሱ ባለስልጣን ግብይቱ በትክክለኛ የገበያ ዋጋ የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፯/ የተላለፈው ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ የሚሰራ እስከሆነ ድረስ የተላለፈለት ሰው ይህንን ገቢ የሚያመነጭ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ራሱ ማካሄዱ አስፈላጊ አይሆንም።

3/ A taxable activity, or part of a taxable activity, shall be a going concern if the activity is operational and capable of being carried on without interruption after the transfer. A taxable activity that is a dormant or prospective business activity is not a going concern.

4/ A taxable activity, or part of a taxable activity, may be a going concern of a registered person even if it is not profitable or the transfer is to a liquidator, receiver, trustee-in-bankruptcy, or other person appointed upon the insolvency of the registered person.

5/ A taxable activity, or part of a taxable activity, transferred by a registered person as a going concern shall qualify as a zero-rated supply only if the transferee has had no previous interest in the taxable activity or the transfer is of an existing taxable activity involving only a change of legal entity or form of undertaking the taxable activity, such as from a partnership to an incorporated company.

6/ When the transferee and the transferor are related persons or if the transferee had a prior interest in the taxable activity, the tax authority may conduct an investigation to ensure that the transaction was made at fair market value.

7/ It shall not be necessary for the transferee to operate the particular income-producing activity acquired, so long as it is capable of separate operation.

፰/ የንግድ የግብርና ስራ አቅርቦት በመካሄድ ላይ ያለ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠረው የቁም እንስሳት፣ የግብርና መሳሪያዎች፣ መገልገያዎች እና ሌሎች የግብርና ንግድ ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉ ሃብቶች የአቅርቦቱ አካል ከሆኑ ነው። የንግድ የግብርና ስራ ብቻውን መተላለፍ በመካሄድ ላይ ያለ የንግድ ስራ እንቅስቃሴ እንደተላለፈ አይቆጠርም።

፱/ በአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፫ አንቀጽ ፩ (ሀ) (v) የተመለከተው ማስታወቂያ የሚሰጥበት የ፵፭ ቀናት ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ስለአቅርቦት ጊዜ የተደነገገውን የሚከተል ይሆናል።

፲/ የተላለፈለት ሰው የማስተላለፉ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ያልተመዘገበ ከሆነ የማስተላለፉ ተግባር ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግለት የተላለፈለት ሰው የማስተላለፉ ተግባር በተፈጸመበት ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሰረት ሲመዘገብ ነው።

፲፩/ አስተላላፊው በአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፫ አንቀጽ ፩ (ሀ) (v) መሰረት ማስታወቂያ ካቀረበ በኋላ የማስተላለፉ ተግባር በመካሄድ ላይ ላለ ድርጅት የተፈቀደው ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የማይደረግለት ሆኖ ቢገኝ፣ የሚከተሉት ተፈጻሚ ይሆናል፦

ሀ) የማስተላለፉ ተግባር የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልበታል፣

ለ) የተላለፈበት ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን የማይጨምር ሆኖ ይወሰዳል፣ እና

ሐ) የተላለፈለት ሰው በአዋጁ በተፈቀደው መሰረት ለአቅርቦቱ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊጠይቅ ይችላል።

8/ The supply of farmland shall be a supply of a taxable activity as a going concern only if supplied with livestock, machinery and equipment, and other assets necessary for the continued operation of agricultural activities on the farmland. The supply of farmland alone is not the supply of a taxable activity as a going concern.

9/ The 45-day period within which the notice referred to in Article 1(a)(v) of Part 3 of Schedule 1 to the Proclamation must be filed shall be determined under the time of supply rules in Article 21 of the Proclamation.

10/ If, prior to the transfer, the transferee was not a registered person, the transfer can qualify for zero rating only if the transferee is registered by the date the transfer takes place as determined under Article 21 of the Proclamation.

11/ If the transferor files the required notice under Article 1(a)(v) of Part 3 of Schedule 1 to the Proclamation and the transfer does not qualify as a zero-rated supply of a going concern under Article 1(a) of Part 3 of Schedule 1 of the Proclamation, the following shall apply:

a) the transfer is subject to VAT;

b) the consideration for the supply shall be treated as being exclusive of VAT; and

c) the transferee can claim an input tax credit in relation to the supply to the extent allowed under the Proclamation.

፲፪/ በአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፫ አንቀጽ ፩ (ሀ) (v) መሠረት ለታክሱ ባለሥልጣን የሚቀርበው ማስታወቂያ የሚከተሉትን ጭምር የሚይዝ መሆን አለበት፡-

ሀ) የተላለፉትን ንብረቶች የተሟላ ዝርዝር፤

ለ) የማስተላለፉ ተግባር በተፈፀመበት ጊዜ እያንዳንዱ የተላለፈው ንብረት የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፤

ሐ) አስተላላፊው ሲያካሂድ የነበረው የንግድ ስራ ባህሪ እና የተላለፈለት ሰው በተላለፈበት ንብረት የሚያካሂደው የንግድ ስራ፤

መ) አስተላላፊው በተላለፉት ንብረቶች የንግድ ስራውን ሲያካሂድ የቆየበትን ጊዜ፤ እና

ሠ) የታክሱ ባለሥልጣን ከአስተላላፊው ወይም ከተላለፈለት ሰው ወይም ከሁለቱም የሚፈልጋቸው ሌሎች መረጃዎች።

፲፫/ አስተላላፊው በመካሄድ ላይ የሚገኘውን የንግድ ስራ እንቅስቃሴ በማስተላለፉ ምክንያት ምዝገባውን የሰረዘ እንደሆነ፤ አስተላላፊው ለተላለፈለት ሰው ያላስተላለፈውን ንብረት በሚመለከት የአዋጁ አንቀጽ ፲፱ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል።

፲፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፲፫ መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፡-

ሀ) አስተላላፊው በእጁ የሚገኙትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች ለተላለፈለት ሰው ያስረክባል፤ የተላለፈለት ሰው እነዚህን ሰነዶች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ሰነዶችን ስለማቆየት ለተደነገገው ጊዜ ያህል ይዞ ያቆያል፤ እና

ለ) አስተላላፊው የንግድ ስራው ባለቤት ሆኖ በቆየበት ጊዜ ለነበረ የተጨማሪ እሴት ታክስ ዕዳ ሁለቱም ወገኖች ኃላፊ ይሆናሉ።

12/The notice to the Tax Authority required under Article 1(a)(v) of Part 3 of Schedule 1 to the Proclamation shall include the following:

a) a complete list of the assets transferred;

b) the fair market value of each asset transferred as at the time of the transfer;

c) the nature of the business carried on by the transferor and the business to be carried on by the transferee with the acquired assets;

d) the length of time the transferor's business has been operated with the assets transferred; and

e) any additional information from the transferor or transferee, or both, as required by the Tax Authority.

13/ If the transferor cancels its registration as part of the transfer of its taxable activity as a going concern, Article 19 of the Proclamation applies to any goods of the transferor not transferred to the transferee.

14/ If an application under Sub-Article (13) of this Article is approved:

a) the transferor shall transfer VAT records to the transferee, and the transferee shall retain those records for the time required for the retention of records under the Tax Administration Proclamation; and

b) both parties are legally obliged to pay any VAT liability incurred while the transferor owned the business.

፲፭/ አስተላላፊው እና የተላለፈለት ሰው የተመዘገቡ ካልሆነ እና በአዋጁ አባሪ ፩ ክፍል ፫ አንቀጽ ፩ (ሀ) (v) መሠረት ሁለቱም ጊዜውን ጠብቀው በማመልከቻው ላይ በመፈረም ካላቀረቡ በስተቀር የተላለፈው በመካሄድ ላይ ያለ ድርጅት ቢሆንም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ አይደረግም።

## ክፍል አስራ አንድ
## ከታክስ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶች

**፶፩. ከታክሱ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶች**

በአዋጁ ከተደነገገው በተጨማሪ ከአዋጁ ጋር በተያያዘው አባሪ ሁለት ተራ ቁጥር ፩ (አ) በተደነገገው መሠረት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው አባሪ ፩ የተዘረዘሩት እቃዎች ወደአገር ሲገቡ እና በአገር ውስጥ ለግብይት ሲውሉ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ተደርገዋል።

**፶፪. የመኖሪያ ቤት**

፩/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ በተተረጎመው መሰረት “ የመኖሪያ ቤት” በመኖሪያ ቤቱ ለመገልገል አስፈላጊ የሆኑትን የመኖሪያ ቤቱን ቅጥር ግቢ እና እንደ መኪና ማቆሚያ፣ መኪና ማሽከርከሪያ፣ የአትክልት ቦታ፣ የተስተካከለ መሬት እና መተላለፊያ ያሉትን መገልገያዎች የሚጨምር ሲሆን፣ ከመኖሪያ ቤቱ ጋር የተያያዘ የእርሻ ቦታን አይጨምርም።

፪/ የሚከተሉት ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች ናቸው፡-

ሀ) በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፩(ሀ) መሠረት ከታክሱ ነፃ የሆኑት የመኖሪያ ቤቶች አካል የሆኑትን የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች መሸጥ፣ ወይም

15/ Unless both the transferor and transferee are registered persons and both sign and file in a timely manner the notice to treat the transfer as a supply of a going concern as required under Article 1(a)(v) of Part 3 of Schedule 1 of the Proclamation, the transfer shall not be a zero-rated supply even if, in fact, it is a transfer of a going concern.

## PART ELEVEN
## EXEMPT SUPPLIES

**51. Tax-Exempt Supplies**

In addition to what is provided under the Proclamation, the goods listed in Annex 1 of this regulation shall be exempt from value-added tax when imported into the country and supplied for trading within the country, in accordance with the provisions of paragraph 1 (p) of Annex Two of the Proclamation.

**52. Residential Premises**

1/ “Residential premises”, as defined in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation, includes the area surrounding or appurtenant to the premises that is necessary for the enjoyment of the premises, but not farmland adjacent to the premises. The land surrounding premises, including driveway, paths, gardens, and landscaped grounds for use and enjoyment of occupants, forms part of the premises.

2/ The following shall be an exempt supply:

a) sale of a parking space that is part of residential premises the supply of which is an exempt supply under Article 1(a) of Schedule 2; or

ለ) በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፩(ሀ) መሠረት ከታክሱ ነጻ የሆኑት የመኖሪያ ቤቶች አካል የሆኑትን የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ማከራየት።

፶፫. **የፋይናንስ አገልግሎቶች**

፩/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፩(ሐ) ለተመለከተው የፋይናንስ አገልግሎት የተከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ግልፅ ወይም በግልፅ ያልተመለከተ ቢሆንም አቅርቦቱ ከታክስ ነፃ ነው።

፪/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ ፊደልተራ (ለ) "ለፋይናንስ አገልግሎት" ለተሰጠው ትርጉም አፈጻጸም "ቼክ" የሚለው ቃል የፖስታ ቤት ትእዛዝን፣ የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝን፣ የመንገደኞች ቼክ ወይም ማናቸውንም ገንዘብ ገቢ ወይም ወጪ የማድረግ ትእዛዝ ወይም ፈቃድ (በጽሁፍ፣ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በሌላ ዘዴ) ለፋይናንስ ተቋም መስጠትን ይጨምራል።

፫/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ "ለፋይናንስ አገልግሎት" በተሰጠው ትርጉም ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሚኒስቴሩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ዝርዝር የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል። ሚኒስቴሩ አዳዲስ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በማከል ወይም በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱትን የፋይናንስ አገልግሎቶች ባህሪ በመቀየር ዝርዝሩን ሊያሻሽል ይችላል። ማናቸውም በዝርዝሩ ላይ የሚደረግ ለውጥ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከወጣበት ቀን በኋላ በሚኖሩ ግብይቶች ላይ ነው።

፬/ ከፋይናንስ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የተሰጡ ቢሆንም ባይሆንም የሚከተሉት የፋይናንስ አገልግሎት አይባሉም፦

ሀ) በፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ለተሰማራ ሰው ወይም በፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ለተሰማራ ሰው ደንበኛ የተሰጡ የህግ፣ ሂሳብ እና የሂሳብ መረጃን የማጠቃለል ወይም የሰነድ አያያዝ፣ የፋይናንስ ስጋትን የመገምገም፣ የሰነድ ማረጋገጫ ወይም የታክስ ወኪል (የታክስ አማካሪነትን ጨምሮ) አገልግሎቶች፣

b) the lease of a parking space as part of the lease of residential premises that is an exempt supply under Article 1(a) of Schedule 2.

53. **Financial Services**

1/ A supply of financial services shall be an exempt supply under Article 1(c) of Schedule 2 of the Proclamation regardless of whether the services are supplied for an explicit or implicit fee.

2/ For the purposes of Paragraph (b) of the definition of "financial services" in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation, the reference to "cheque" includes a postal order, money order, traveller's cheque, or any order or authorisation (whether in writing, by electronic means, or otherwise) to a financial institution to credit or debit any account.

3/ In addition to the services listed as financial services in the definition of "financial services" in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation, the Minister may issue a directive listing financial services. The Minister may modify the list, including making changes required by the introduction of new financial services or modification of the nature of services specified in the list. Any changes to the list shall have prospective effect only.

4/ The following services shall not be financial services whether or not supplied in connection with financial services:

a) legal, accounting and record package services, actuarial, notary, and tax agency services (including advisory services) when rendered to a supplier of financial services or to a customer of that supplier of financial services;

ለ) ጥሬ ገንዘብ፣ ሰነድ ወይም ሌላ ነገር በአደራ ማስቀመጥ፣

ሐ) መረጃን የማቀነባበር እና የደመወዝ ክፍያ አገልግሎት፣

መ) ዕዳ የመሰብሰብ ወይም ተሰብሳቢ ሂሳብን መሸጥ፣

ሠ) የጡረታ መዋጮ ፈንድን ማስተዳደርን የመሳሰሉ የአስተዳደር ስራዎች፣

ረ) የባለአደራ፣ የፋይናንስ ምክር እና የሀብት አስተዳደር ዕቅድ የማውጣት አገልግሎቶች፣ እና

ሰ) ከፋይናንስ ሰነዶች ውጭ ያሉ ንብረቶችን የማከራየት፣ ፈቃድ የመስጠት እና ተመሳሳይ የማመቻቸት ስራዎች፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ሀ) የተመለከተው “ሂሳብ እና የሂሳብ መረጃን የማጠቃለል ስራ” ሂሳብ በማወራረድ ሂደት በፋይናንስ ተቋማት የተከናወኑ የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን የማስታረቅ ስርአትን፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን በደንበኞች ሂሳብ ላይ መመዝገብን፣ የደንበኞችን ሂሳብ ማስተዳደርን እና በንዑስ አንቀጽ (፬) ከተዘረዘሩት አገልግሎቶች ጋር ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን መስጠትን ይጨምራል።

፮/ ተሰብሳቢ ሂሳብን በመግዛት ብድር መስጠትን ጨምሮ እዳን መግዛት ብቻውን የፋይናንስ አገልግሎት እንደሆነ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ ተሰብሳቢ ሂሳብን ከመግዛት ጋር የተያያዘውን የሽያጭ ሂሳብ አያያዝ አገልግሎት እና ተሰብሳቢ ሂሳብን ከመግዛት ጋር የተያያዙ ሌሎች አገልግሎቶችን ጨምሮ እዳውን ከማስመለስ፣ ከክስ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች እና ከባለእዳዎች ላይ የሚፈለገውን ገንዘብ ለማስመለስ የሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት የፋይናንስ አገልግሎት አይባሉም።

b) safe custody of cash, documents, or other items;

c) data processing and payroll services;

d) debt collection or factoring services;

e) management services, such as management of a superannuating fund;

f) trustee, financial advisory, and estate planning services, and

g) leases, licences, and similar arrangements relating to property other than a financial instrument.

5/ The reference to “accounting and record packaging services” in Sub-Article (4)(a) of this Article includes a financial clearing system that may be part of the settlement process, the posting of financial transactions to customers' accounts, the maintenance of customers' accounts, and the rendering of services ancillary to the services referred to in Sub-Article (4).

6/ The mere acquisition of a debt shall be a financial service, including a debt acquired by a factor. The services related to debt recovery, litigation, and the management of the recovery of the amount due from debtors shall not be financial services, including sales accounting services under a factoring arrangement and other services related to factoring.

፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እና ከታክሱ ነጻ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ከሆነ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የተመለከተውን የማከፋፈያ ዘዴ መሰረት በማድረግ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክሶችን እንዲያከፋፍል የታክሱ ባለስልጣን ሊፈቅድ ይችላል።

፰/ የግብአት ታክስን ለማከፋፈል የትኛውም ዘዴ በጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም፣ የፋይናንስ አገልግሎትን የሚያቀርብ የተመዘገበ ሰው የተከተለው ተገቢውን ዘዴ መሆኑን የሚያረጋጡ ማስረጃዎችን መያዝ አለበት። የታክሱ ባለስልጣን የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች የእያንዳንዱን የአቅርቦት ዘርፍ ስታትስቲካዊ መረጃ እንዲያቀርቡ ሊያዝ ይችላል።

፱/ ከታክሱ ነፃ በሆነው የኢንሹራንስ ዋስትና ፖሊሲ ሽፋን የሚካተቱ ከታክሱ ነጻ ከሆነው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር ያልተያያዙ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች እነዚህ አገልግሎቶች ለብቻቸው ቢሰጡ ሊከፈል በሚገባው ታክስ ልክ ታክሱን እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። የታክሱ ባለስልጣን የኢንሹራንሱ ፖሊሲ አካል ያልሆነው አገልግሎት ከዋናው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር የተያያዘ ተጨማሪ አገልግሎት መሆን ያለመሆኑን የመወሰን ሙሉ ስልጣን አለው።

፲/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ “ለፋይናንስ አገልግሎት” በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈን የኢንሹራንስ ፖሊሲ አቅርቦት ከታክሱ ነጻ የሆነ አቅርቦት ሊሆን የሚችለው ፖሊሲው የተሰጠው በኢንሹራንስ ስራ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፮/፪ሺ፲፪ (እንደተሻሻለ) ፈቃድ በተሰጠው ሰው ሲሆን ነው።

7/ Notwithstanding Article 29 Sub-Article (2) of the Proclamation, where a registered person makes both taxable supplies and exempt supplies of financial services, the Tax Authority may approve the registered person using a method of apportionment of input tax in accordance with guidelines specified in a Directive issued by the Minister of Revenue.

8/ Regardless of the method used to apportion input tax credits, a registered person making supplies of financial services shall maintain records to substantiate the method used. The Tax Authority may require suppliers of financial services to submit statistical data on various product lines.

9/ Services covered in riders to exempt insurance policies that are not incidental to the insurance coverage shall be taxable to the extent that the independent supply of those services would be taxable. The Authority shall have the sole discretion to determine whether a non-insurance rider is incidental to the main insurance policy.

10/ The supply of an insurance policy within the definition of “financial services” in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation shall be an exempt supply only if the policy is issued by a person who is licensed to issue such policies under the Insurance Business Proclamation No. 746/2012.

፲፩/ ለደንበኞቻቸው የኢንሹራንስ ሽፋን ለማስገኘት የሚሰሩ የኢንሹራንስ ደላሎች ወይም ወኪሎች የሚያገኙት ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ እንደ ፋይናንስ አገልግሎት የማይቆጠር በመሆኑ ለኢንሹራንስ በተሰጠው የታክስ ነጻ መብት አይሸፈንም።

፲፪/ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ለንብረት ጥራት ወይም አፈፃፀም ዋስትና የሚገባ የኢንሹራንስ ሽፋንን አይጨምርም።

፲፫/ በአዋጁ ለፋይናንስ አገልግሎት የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ድርጅቶች እና የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተሮች የሚያከናውኑትን አቅርቦት አይጨምርም፡፡

**፶፬. የዋስትና ሰነዶች እና የፋይናንስ አገልግሎቶች**

፩/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ ፊደል ተራ (መ) “ለፋይናንስ አገልግሎት” በተሰጠው ትርጉም የተመለከተው የዋስትና ሰነዶችን የመገበያየት ተግባር ከታክሱ ነፃ የሆነ ግብይት ነው። ይሁን እንጂ የዋስትና ሰነዶችን የመገበያየት ተግባር ከአቅርቦቱ ተግባር ጋር የተያያዙ የማስታወቂያ፣ የህትመት ወጪዎችን፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የህግ እና የምክር አገልግሎቶችን አይጨምርም።

፪/ “የፋይናንስ አገልግሎት” ዋንኛ ስራቸው የአክሲዮን ባለቤቶችን፣ የአባላትን ወይም የሌሎች ሰዎችን ገንዘብ ኢንቬስት የማድረግ ተግባር ለሆነ የንግድ ስራዎች የሚሰጥ የስራ አመራር ወይም የአስተዳደር ተግባርን አይጨምርም።

**፶፭. የእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት**

፩/ ይህ የደንቡ ክፍል በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ ተራ ቁጥር (፩) “ለፋይናንስ አገልግሎት” ለተሰጠው ትርጉም አፈጻጸም የሚያገለግል ነው።

11/ Commissions and other fees earned by brokers or agents who provide insurance coverage for their customers shall not come within the exemption for insurance as a financial service.

12/ An insurance policy shall not include insurance cover on a warranty in respect of the quality, or performance of tangible property.

13/ The tax exemption granted to financial services by the Proclamation does not include the provision of payment instrument issuers and payment system operators.

**54. Securities and Financial Services**

1/ The underwriting of the issuance of securities referred to in paragraph (d) of the definition of “financial services” in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation shall be an exempt supply. However, the exemption for underwriting services shall not extend to other services obtained in connection with an underwriting, such as advertising and printing costs, accounting, legal, and advisers' fees.

2/ “Financial services” shall not include management or administrative services provided to a business whose principal activity is investing funds for shareholders, members, or other persons.

**55. Islamic Financial Services**

1/ This Regulation shall apply for the purposes of Paragraph (l) of the definition of “financial services” in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation.

፪/ ሚኒስቴሩ ስለእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት የተደነገጉትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የሚከተሉትን ተግባራዊ ያደርጋል፡-

ሀ) የፋይናንሱ ስራ የሚያካትታቸውን የተለያዩ አቅርቦቶች ለይቶ ማወቅ፤

ለ) በእስልምና የፋይናንስ ስራ ውስጥ የማይካተቱ አቅርቦቶችን የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም መወሰን፤ እና

ሐ) በእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት የሚቀርቡ አገልግሎቶች አንድ ዓይነት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም እንዲኖራቸው ማድረግ።

፫/ ለእስልምና የባንክ አገልግሎት አቅርቦቶች የሚኖረው የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም እስልምና ነክ ካልሆኑ የባንክ አገልግሎት አቅርቦቶች ጋር ዕኩል ካልሆነ፣ የተጨማሪ እሴት ታክሱ አፈፃፀም የአቅርቦቱን አላማ፣ ባህሪያት እና ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰናል።

፬/ ሚኒስቴሩ የአንድን የእስልምና የባንክ አገልግሎት አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀጽ "የእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት" ማለት የሸሪያ ህግ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ የፋይናንስ አቅርቦት አገልግሎት ውል ነው።

## ፶፮. የኃይማኖት ነክ አገልግሎት

፩/ ለአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፩(ቀ) አፈጻጸም በሃይማኖት ተቋም የሚሰጡ የኃይማኖቱ ሥርዓት አንድ ክፍል የሆኑ አቅርቦቶች የኃይማኖት ነክ አገልግሎት ይባላሉ።

2/ The Ministry shall implement the following measures to implement the provisions of the Proclamation on Islamic Financial Services:

a) identify the different supplies made under the arrangement;

b) determine the VAT treatment of those supplies if they had not been made under an Islamic financial arrangement; and

c) Apply the same VAT treatment to the supplies made under the Islamic financial arrangement.

3/ If a supply made under an Islamic financial arrangement does not have a direct equivalent in VAT treatment with a non-Islamic financial arrangement, the VAT treatment shall be determined by having regard to the underlying purposes, features, and circumstances of the supply.

4/ The Minister may issue a Directive specifying the VAT treatment of a particular Islamic financial arrangement.

5/ In this Article, "Islamic financial service" means a contractual arrangement relating to the supply of finance in accordance with the principles of Syariah law.

## 56. Religious related Services

1/ Services supplied by a religious organisation that are integral to the practice of the religion of the organisation shall be treated as religious or church-related services for the purposes of Article 1(h) of Schedule 2 of the Proclamation.

፪/ የኃይማኖት ተቋም የሚያቀርባቸው እና ከግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ጋር ተወዳዳሪ የሆኑ አቅርቦቶች ወይም የሃይማኖቱ ስርአት አካል ያልሆኑ አቅርቦቶች የሃይማኖት ነክ አገልግሎት አይባሉም። የኃይማኖቱ ተቋም የሚያቀርባቸው የዚህ ዓይነት አቅርቦቶች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ለምዝገባ ከተቀመጠው የገንዘብ በላይ ከሆነ የኃይማኖት ተቋሙ ለምዝገባ ማመልከቻ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፫/ በጥሬገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሰጥ እርዳታ (እንደ ሙዳየ ምጽዋት ያለ) ወይም አገልግሎት፣ በዕርዳታው እና የእርዳታ ሰጪው በሚያገኘው ጥቅም መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ከሌለ በስተቀር የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም።

፬/ የኃይማኖት ተቋም ከንግድ ድርጅት የሚቀበለው ገንዘብ የሰጪው ስም በመጽሄት ወይም በፕሮግራም እንዲጠቀስ የሚያስችል ቢሆንም ለአቅርቦት የተከፈለ ዋጋ እንደሆነ አይቆጠርም። ሆኖም የሃይማኖት ተቋሙ በመጽሄት ወይም በፕሮግራም ውስጥ ቦታ ለመሸጥ ክፍያ የተቀበለ ከሆነ ክፍያው ለአቅርቦት የተፈጸመ ክፍያ እንደሆነ ስለሚቆጠር ለኃይማኖት ነክ አገልግሎት በተሰጠው ከታክስ ነፃ የመሆን መብት አይሸፈንም።

፭/ በልማት ኮሚሽን ወይም ተመሳሳይ ተቋም ወይም በቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል አማካኝነት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሚያከናውን የሃይማኖት ተቋም፣ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ያለው ኮሚሽን፣ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተናጠል ምዝገባ እንዲያደርግ እንዲፈቀድለት ሊያመለክት ይችላል።

2/ The supply of services by a religious organisation that compete with the private sector or that are not integral to the practice of the religion shall not be treated as religious related services. If the value of the taxable supplies made by a religious organisation exceeds the registration threshold under Article 12 of the Proclamation, the religious organisation shall be liable to apply for registration.

3/ The donation in kind or money (such as church plate donations) or services shall not be subject to VAT provided there is no direct link between the payment and any benefit received by the donor.

4/ A receipt by a religious organisation from a business shall not be a supply for consideration if the receipt merely entitles the transferor to be mentioned in a brochure or program, but if a religious organisation receives payment when it sells space in a brochure or program, the receipt shall be a supply for consideration that does not come within the exemption for religious or church-related services.

5/ A religious organisation that undertakes taxable activities through a development commission or similar entity, or through a division or branch, may apply for, or be required to separately register one or more of the commissions, divisions, or branches as provided under Directive issued by the Minister of Revenue.

**፶፯. የታወቀ የህክምና ተቋም**

በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ "ለታወቀ የህክምና ተቋም" ለተሰጠው ትርጉም አፈጻጸም" "የታወቀ የህክምና ተቋም" ፈቃድ የተሰጠውን የህክምና ባለሙያ፣ ሆስፒታልን፣ የማዋለጃ ክሊኒክን፣ የአረጋውያን እንክብካቤ መስጫን ወይም የህክምና ክሊኒክን ይጨምራል።

**፶፰. የታወቀ የህክምና አገልግሎት**

፩/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ "ለህክምና አገልግሎት" ለተሰጠው ትርጉም አፈጻጸም" "የታወቀ የህክምና አገልግሎት" ማለት በሽታን ወይም ሌላ ህመም የመመርመር፣ የማከም፣ የመከላከል፣ ወይም የማገገም እና የአእምሮ ደህንነትን የመንከባከብ አገልግሎት ነው። የሕክምና አገልግሎት በክፍያ የተሰጠ ከሆነ ከፋዩ ተመላላሽ ታካሚው፣ ተኝቶ የሚታከመው ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ቢሆንም ባይሆንም የታወቀ የህክምና አገልግሎት ይሆናል።

፪/ ምግብ እና መኝታ ማቅረብ፣ የአረጋውያን እንክብካቤ እና የግል የህክምና እንክብካቤ እና በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚደረግ ድጋፍን ጨምሮ፣ የታወቀ የህክምና ባለሙያ ለተመላላሽ ወይም ተኝቶ ለሚታከም ታካሚ በታወቀ የህክምና ተቋም ውስጥ የሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት የታወቀ የሕክምና አገልግሎት ይባላል።

፫/ የሚከተሉት የታወቀ የህክምና አገልግሎት እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ፦

ሀ) የተለየ ክፍያ የማይጠየቅባቸው በታወቀ የሕክምና አገልግሉት የሚቀርቡ መድኃኒቶች፣

ለ) የላቦራቶሪ፣ የኤክስሬይ ወይም ሌላ የምርመራ አገልግሎት፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን የህክምና አገልግሎቶች በመስጠት ሂደት የሚቀርቡ የህክምና መገልገያዎች፣

**57. Qualified Medical Facility**

For the purposes of the definition of "qualified medical facility" in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation, "qualified medical facility" includes the offices of a licensed medical practitioner, a hospital, maternity or nursing home, or medical clinic.

**58. Qualified Medical Services**

1/ For the purposes of the definition of "medical services" in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation, "qualified medical services" means the diagnosis, treatment, prevention, or amelioration of a disease or other illness, and the promotion of mental health. Medical services are qualified medical services regardless of whether they are provided with or without charge, and, if provided for charge, regardless of whether the charge is paid by the patient, resident, or a third party.

2/ Services provided by a qualified medical practitioner to a patient or resident in a qualified medical facility shall be qualified medical services, including the supply of meals and accommodation, nursing and personal care, assistance with daily living activities to meet the needs of the resident or patient.

3/ The following are treated as qualified medical services:

a) the supply of medicines and drugs in a qualified medical facility for which there is no separate charge;

b) a laboratory, X-ray, or other diagnostic service;

c) the supply of medical devices as part of the supply of qualified medical services referred to Sub-Article (1) of this Article;

መ) የሕክምና መሳሪያዎች ወይም አቅርቦቶችን ጨምሮ በኦፐራሲዮን ክፍል፣ በምርመራ ክፍሎች እና በማደንዘዣ ክፍሎች የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

ሠ) የታወቀ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ሂደት የሚከናወኑ የራዲዮቴራፒ፣ የፊዚዮቴራፒ እና የአእምሮ እድገት ህክምና፣ አገልግሎቶች፣

ረ) ታካሚ ላልሆኑ ሰዎች የሚሰጠውን የሬስቶራንት ወይም የካፊቴሪያ አገልግሎት ሳይጨምር ለተመላላሽ እና ተኝተው ለሚታከሙ ታካሚዎች የሚሰጥ የመኝታ እና የምግብ አገልግሎት፣

ሰ) ከታወቀ የሕክምና ተቋም ጋር በተያያዘ አገልግሎት የሚሰጡ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እና ቴክኒሽያኖችን ጨምሮ በታወቀ የህክምና ተቋም ሠራተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

ሸ) አጠቃላይ የጥርስ ሕክምናን ወይም ጥርስ ማስጌጥን ሳይጨምር ከበሽታ፣ ከጭንቀት ተሞክሮ ወይም ከተፈጥሮ መዛባት ጋር በተያያዘ የሚሰጥ የጥርስ ህክምና፣ የጥርስ ደጋፊ አካላት እና የጥርስ የውስጥ ክፍል ህክምና፣ እና

ቀ) ሥነ-አዕምሮአዊ ትንተና።

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) (ሐ) አፈጻጸም "የሕክምና መገልገያ" ማለት የታወቀ የሕክምና አገልግሎት በመስጠት ሂደት፣ በታወቀ የሕክምና ተቋም ውስጥ ለተመላላሽ ወይም ተኝቶ ታካሚው አገልግሎት የሚሰጥበት ወይም በሐኪም ትዕዛዝ ለታካሚው የሚሰጥ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ) የአተነፋፈስ ወይም የልብ ምት መከታተያ፣ የኩላሊት ማጠቢያ መሳሪያ ወይም የአካል ጉዳተኞች መመገቢያ ቁሳቁስ፣

d) the use of operating rooms, case rooms, or anaesthetic facilities, including necessary equipment or supplies;

e) the use of radiotherapy, physiotherapy, or occupational therapy facilities in supplying qualified medical services;

f) accommodation and meals supplied to patients or residents in the course of receiving qualified medical services, but not including meals provided in a restaurant or cafeteria available to persons other than patients and residents;

g) services supplied by staff of a qualified medical facility, including orderlies and technicians, in connection with qualified medical services;

h) dental, periodontal, and endodontic services supplied in connection with a disease, trauma, or congenital deformity, but not for general dentistry or cosmetic purposes; and

i) Psychoanalytic services.

4/ For the purposes of Sub-Article (3)(c) of this Article, "medical devices" means devices supplied to a resident or patient in a qualified medical facility, or supplied on prescription in connection with the supply of qualified medical services, including:

a) a respiratory or heart monitor, dialysis machine, or feeding utensil for use by an individual with a disability;

ለ) የታወቀ የህክምና አገልግሎት አካል ሆኖ በህክምና ወይም በኦፕራሲዮን ሂደት የሚሰጥ ሰው ሰራሽ የሰውነት አካል ወይም የአካል ድጋፍ መሳሪያ፣ እና

ሐ) ለታወቀ የህክምና ተቋም የሚቀርብ የህክምና ወይም የኦፕራሲዮን መሳሪያ ወይም ለተመላላሽ ወይም ተኝቶ ለሚታከም ሰው የሚሸጥ ወይም በኪራይ የሚቀርብ ተመሳሳይ መሳሪያ፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ውስጥ "የታወቀ የህክምና ባለሙያ" አግባብ ባለው የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ተቋም በጤና ባለሙያነት ወይም በሕክምና ባለሙያነት እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው። ይህም በጤና ዶክተሮችን፣ አካሚዎችን፣ የጤና ኦፊሰሮችን፣ ፊዝዮቴራፒስቶችን እና ሌሎች የጤና አገልግሎት ሰጪዎችን ይጨምራል።

## ፶፱. የትምህርት ፕሮግራም

፩/ ለትርፍ የተቋቋመ ወይም ለትርፍ ያልተቋቋመ ቢሆንም በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፪ "ለትምህርት ፕሮግራም" የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟላ የትምህርት ኮርስ በአዋጁ ይሸፈናል።

፪/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ 2 "ለትምህርት ፕሮግራም" ለተሰጠው ትርጉም አፈፃፀም የትምህርት ፕሮግራም አካል ሆነው ይቆጠራል፡-

ሀ) በታወቀ የትምህርት ተቋም ለተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት፣

ለ) በታወቀ የትምህርት ተቋም የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም አካል ሆነው በአይነት የሚቀርቡ የምግብ እና ሌሎች ተዛማጅ እቃና አገልግሎቶች፣

ሐ) በታወቀ የትምህርት ተቋም የተሰጠ እስከሆነ ደረስ ስለፈተና የሚደረግ ገለጻ ወይም የፈተና አስተዳደር፣

b) a medical or surgical prosthesis or orthopaedic aid supplied as part of a qualified medical service; and

c) Medical or surgical equipment supplied to a qualified medical facility, or the sale or rental of such equipment to a patient or resident.

5/ In this Article, "qualified medical practitioner" means a person licensed by the appropriate federal or state government agency to practice as a health professional or medical professional. This includes doctors; nurses; health officers; physiotherapists and other health service providers.

## 59. Education Course

1/ A course of study can qualify as an "education course" as defined in Article 2 of Schedule 2 regardless of whether the educational institution provides the course on a for profit or not-for-profit basis.

2/ The following are treated as part of an education course for the purposes of the definition of "education course" in Article 2 of Schedule 2 of the Proclamation:

a) a course of instruction provided to students at a qualified education institution;

b) qualified meal plans, and other associated goods or services provided in kind as part of the education program provided by a qualified education institution;

c) instruction in, or the administration of examinations, provided by the qualified educational institution;

መ) ከታወቀ የትምህርት ኮርስ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ትምህርት ወይም ማስጠናት፣ እና

ሠ) ከትምህርት ቤቱ ጋር በተደረገ ውል በሚሰራ የግል ድርጅት ሳይሆን በትምህርት ቤቱ በራሱ የሚሰጥ ተማሪዎችን ከቅደመ- አንደኛ ደረጃ፣ ከአንደኛ ደረጃ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደቤታቸው እንዲሁም ከቤታቸው ወደትምህርት ቤቱ በማመላለስ የሚሰጥ የትምህርት ቤት የትራንስፖርት አገልግሎት፡፡

፫/ የሚከተሉት ክፍያዎች ለትምህርት ፕሮግራም አቅርቦት የተፈጸሙ ክፍያዎች ሆነው ይቆጠራሉ፦

ሀ) ከትምህርቱ፣ ከአገልግሎት መስጫዎች እና ከካሪኩለም ጋር ለተያያዙ ተግባራት የሚፈፀም ክፍያ፣

ለ) የታወቀው የትምህርት ተቋም ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ ለሚያቀርባቸው መገልገያዎች የሚያስከፍላቸው አስገዳጅ የሆኑ ክፍያዎች፣

ሐ) የተማሪዎች ምክር ቤት ክፍያ፣ የስፖርት ቡድን ክፍያ እና ሌሎች ከትምህርት ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ አስገዳጅ ክፍያዎች፣

መ) ከትምህርት ፕሮግራም ጋር በቀጥታ በተያያዘ ሁኔታ የታወቀው የትምህርት ተቋም ለሚሰጣቸው የተማሪ ሪፖርት፣ የመጽሃፍት ቤት አገልግሎት፣ የመታወቂያ ካርድ፣ የመረጃ አያያዝ እና ሌሎች የአስተዳደር አገልግሎቶች የሚፈጸም ክፍያ፣

d) instruction or tutoring related to a qualified education course; and

e) school bus transportation to and from a pre-primary, primary, or secondary school if it is provided by the school authority but not if provided by a private company under contract with the school authority.

3/ The following amounts are treated as part of the consideration for a supply of an education course:

a) charges for tuition, facilities, and curriculum related activities and instruction;

b) compulsory levies for facilities provided by a qualified education institution in relation to an education course;

c) student council fees, athletic fees, and other mandatory fees related to course registration;

d) charges for reports, library services, identity cards, record keeping, and other administrative services provided by a qualified educational institution and directly related to the supply of education courses;

ሠ) ለትምህርት አገልግሎት መሣሪያዎች የሚከፈል ክፍያ፣ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ዕቃዎችን (ለምሳሌ የሙዚቃ መሣሪያዎችን መከራየት) በትምህርቱ አቅራቢ ማከራየት፣ እና በቀጥታ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር የተያያዙ እና በዋናነት መዝናኛ ያልሆኑ የመስክ ጉዞዎችን

ረ) በታወቀ የትምህርት ተቋም የሚቀርቡ የተማሪ ማረፊያዎች (ሆስቴሎችን ጨምሮ)፤ እና፣

ሰ) ለህንፃዎች፣ የግቢዎች፣ የቤተ-መፃሕፍት እና የኮምፒውተር፣ ሳይንስ እና ሌሎች የላቦራቶሪዎችን የመገልገያ ክፍያዎችን ያካትታል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉት ከቅደመ አንደኛ ደረጃ፤ የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ ክፍያዎች የትምህርት ፕሮግራም ክፍያዎች ሆነው ይወሰዳሉ፡-

ሀ) የልዩ ትምህርትን ጨምሮ ለመሰረታዊ ትምህርቶች የሚፈፀም ክፍያ፤

ለ) ትምህርት ቤት ከሚያካሂደው የትምህርት ፕሮግራም በተያያዘ ለቅድመ አንደኛ ወይም ለድህረ ትምህርት ፕሮግራሞች የሚፈጸም ክፍያ፣

ሐ) በትምህርት ቤቱ የሙዚቃ ወይም የስፖርት መሳሪያዎች ለመጠቀም የሚፈፀም ክፍያ፤

መ) የትምህርቱ ፕሮግራም አካል ለሆነ በተማሪዎች ወይም በመምህራን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚፈጸም ክፍያ፤ እና

ሠ) የትምህርት ቤት ቲያትር፤ ዳንስ፤ ጉዞ ወይም ሌላ በዋንኛነት ለተማሪዎች ለተዘጋጀ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ የሚፈፀም ክፍያ፤

e) charges for course materials, the rental of curriculum-related goods by the supplier of the education course (e.g., the rental of musical instruments), and field trips directly related to the curriculum if not predominantly recreational;

f) student accommodations (including hostels) supplied by a qualified education institution; and

g) Qualified facility charges include charges for buildings, grounds, libraries, and computer, science, and other laboratories.

4/ In addition to the amounts specified in Sub-Article (3) of this Article, the following amounts are treated as part of the consideration for a supply of an education course by a pre-primary, primary, and secondary school:

a) basic instruction, including special education courses;

b) fees or charges for a pre-school or after-school program operated by the school;

c) charges for the use of school musical instruments or sports equipment;

d) fees for services rendered by students or their teachers as part of the instructional program; and

e) Charges for students to attend a school play, dance, field trip, or other school-sanctioned activity primarily for the students.

፭/ በዩኒቨርሲቲ ወይም በቴክኒክ ኮሌጅ የሚሰጥ ከታክሱ ነጻ የሆነ የትምህርት አገልግሎት ተማሪው ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ለማግኘት የሚማር ባይሆንም በርቀት ወይም በርቀት ግንኙነት የሚሰጡ ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ ኮርሶችን ይጨምራል።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) ከተመለከተው በተጨማሪ የሚከተሉት ለአዋቂ ትምህርት፤ ለሙያ ትምህርት እና ለቴክኒክ ትምህርት፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለአእምሮ ጉዳተኞች ስልጠና የሚከፈሉ ክፍያዎች ሆነው ይወሰዳሉ፡-

ሀ) ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ የአዋቂ የትምህርት ኮርሶች ወይም የኮርሱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎችን ከቅጥር ጋር የተያያዙ ክህሎቶች ለማዳበር ለሚያስፈልጉ ኮርሶች የሚከፈል ክፍያ፤

ለ) የተማሪዎችን የሙያ ክህሎት ለማዳበር ለሚያግዙ በሙያ ትምህርት ቤቶች ለሚሰጡ የሙያ ኮርሶች የሚከፈል ክፍያ፤

ሐ) አግባብ ባለው የመንግሥት እውቅና ሰጪ ተቋም የሙያ ወይም የንግድ ስራ እውቅና ወይም ስያሜ ለማግኘት ወይም ይህ ማረጋገጫ እንዲቀጥል ለማድረግ ወይም የሙያ ማሻሻያ ለማድረግ ለሚሰጡ ኮርሶች የሚፈጸም ክፍያ፤ እና

መ) የዕውቅና ወይም የስያሜ ኮርስ ወይም ፕሮግራም የምስክር ወረቀት ለማግኘት ወይም ፈተና ለመውሰድ የሚፈጸም ክፍያ።

5/ Exempt education services supplied by a university or technical college shall include courses, including correspondence courses and courses provided remotely, that qualify for credit toward a degree or diploma, whether or not the student is pursuing a degree or diploma program.

6/ In addition to the amounts specified in Sub-Article (3) of this Article, the following amounts are treated as part of the consideration for a supply of an adult education, vocational training, and technical education course, and a course for the education or training of physically or mentally handicapped persons:

a) fees for adult education courses leading to a degree or diploma or courses that are likely to enhance employment-related skills of the students enrolled in the courses;

b) fees for courses of study at a vocational school that develop or enhance a student's occupational skills;

c) fees for courses leading to, or to maintain or upgrade, a professional or trade accreditation or designation recognised by the appropriate government accrediting agency; and

d) Fees for a certificate or examination in a course or program for accreditation or designation.

፯/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) አፈፃፀም አንድ ኮርስ ከቅጥር ጋር የተያያዘን ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል ነው የሚባለው የኮርሱ አላማ ተማሪዎች የሚያገኙትን ክህሎት ለይቶ የሚያሳይ እና ተማሪዎች ያገኙትን ክህሎት ለመዝናኛ፣ ለግል ፍላጎት ማርኪያ፣ ለኪነጥበብ ወይም ባህላዊ ዓላማዎች ሳይሆን ለቅጥር፣ ለንግድ ስራ ወይም ለሙያ ስራ የሚጠቀሙበት ከሆነ ነው።

፰/ የሚከተሉት ኮርሶች አቅርቦት የትምህርት ኮርስ አቅርቦት ነው አይባልም፦

ሀ) ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ የሚያስገኝ ካልሆነ በስተቀር የስፖርት፣ የጨዋታ፣ የቪዲዮ ቀረጻ ወይም የፎቶግራፍ ወይም ሌላ የግል ፍላጎትን የሚመለከቱ ወይም የመዝናኛ ኮርሶች፣

ለ) ለግል መገልገያ ወይም መጠቀሚያ የሚውል የስእል፣ የምግብ ዝግጅት፣ የመኪና መንዳት፣ የፀጉር ስራ እና ሌሎች የውበት መጠበቂያ ኮርሶች፣ እና

ሐ) የትምህርት ካሪኩለም አካል ያልሆነ የሙዚቃ ትምህርት።

፱/ የሚከተሉት የትምህርት ፕሮግራም አቅርቦት አካል ሆነው አይወሰዱም፦

ሀ) የትምህርት ተቋም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውጪ ላለ ቡድን የሚሰጠው የኪራይ አገልግሎት፣

ለ) የትምህርት ቤቱን የስፖርት ውድድር ለሚከታተል አጠቃላይ ማህበረሰብ የመግቢያ ቲኬት መሸጥ፣

ሐ) በትምህርት ቤቱ ይዞታ ውስጥ በሳንቲም የሚሰሩ መሳሪያዎችን ከሚያስቀምጡ የሚገኝ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ፣ እና

7/ For the purposes of Sub-Article (6) of this Article, courses are treated as enhancing employment-related skills if the course objectives specify those skills that students will acquire, and there is a reasonable expectation that the skills taught will be used by the students in their employment, businesses, professions, or trades, rather than for recreational, hobby, artistic, or cultural purposes.

8/ The supply of the following courses shall not be education courses:

a) a course in sports, games, video recording or photography or other hobbies or recreational pursuits, unless they are part of a degree-or diploma-granting program;

b) a course, such as picture framing, cooking, driving, hairdressing and other personal grooming, and personal investment, that is undertaken for personal purposes or benefit; and

c) Music lessons that are not part of a school curriculum.

9/ The following shall not be part of a supply of an education course:

a) the rental of facilities by an educational institution to an outside group;

b) the sale of admission to school athletic events open to the general public;

c) commissions and other fees received from the placement of coin-operated machines on the institution's property; and

መ) የትምህርት ቤቱን አርማ የያዙ ዕቃዎችን እና የመሳሰሉትን ከትምህርት ጋር ግንኙነት የሌላቸውን እቃዎች በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፡፡

፲/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ የእምነት ተቋማት ሰራተኞች ተማሪ ሆነው ይወሰዳሉ።

፷. **የአካል ጉዳተኞችን የሚቀጥሩ ሰዎች**

፩/ የአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፩ (ኘ) የአካል ጉዳኞችን ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞችን ቀጥረው በሚያሰሩበት ድርጅት የዕቃ እና የአገልግሎት አቅርቦት በማከናወን ላይ ለሚገኙ ሰዎች ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/ በአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፩ (ኘ) የተደነገገው የ፷% ተፈላጊ መስፈርት ከአጠቃላይ የድርጅቱ ሠራተኞች መካከል የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞችን ብዛት በመቶኛ በመውሰድ የሚሰላ ሲሆን፤ ይህ ቁጥር ሁልጊዜም የተሟላ መሆን አለበት። ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ዓላማ "ሠራተኛ" ቋሚ፤ የከፊል ጊዜ እና ጊዜያዊ ሠራተኛን ይጨምራል።

፷፩. **ሰብአዊ ዕርዳታ**

የአዋጁ አባሪ ፪ አንቀጽ ፩ (ተ) እና የአባሪ ፫ ፊደል ተራ (ነ) የአደጋ መከላከል የብሔራዊ የስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ወይም ማንኛውም ተተኪ ድርጅት የተፈጥሮ አደጋ፤ የኢንዱስትሪ አደጋ ወይም ሌላ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ባደረገው ጥሪ መሠረት ወደአገር ለሚገቡ እና በአገር ውስጥ ለሚቀርቡ ዕቃዎች ተፈፃሚ ይሆናል።

d) The sale of non-course material, such as items containing the school logo.

10/ Religious workers receiving education shall be treated as students for purposes of this Article.

60. **Persons Employing the Disabled**

1/ Article 1 (o) of Schedule 2 of the Proclamation shall apply to persons supplying goods and services employing physically and mentally disabled individuals.

2/ The 60% requirement specified in Article 1 (o) of Schedule 2 of the Proclamation shall be determined by reference to the number of disabled employees as a percentage of the total employees and shall be satisfied at all times. For the purpose of tis sub-article, "employee" includes full-time, part-time, and casual employees.

61. **Humanitarian Aid**

1/ Article 1(r) of Schedule 2 and Paragraph (m) of Schedule 3 of Proclamation shall apply to the supply or import of goods for rehabilitation purposes after the announcement or declaration of a natural disaster, industrial accident, or catastrophe by the National Disaster Risk Management Commission or any successor organisation.

## ክፍል አስራ ሁለት

## ከታክሱ ነጻ የሆኑ ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች

**፷፪. ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲውል ወደ ሀገር የሚገባ ወርቅ**

የወርቁ የጥራት ደረጃ ወይም የሚቀርብበት ቅርጽ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ወደ ሀገር ገብቶ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ በአዋጁ አባሪ ፫ አንቀጽ ፩(ሰ) መሠረት ከታክሱ ነፃ ይሆናል።

## ክፍል አስራ ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፷፫. የደንቡን ክፍል ስድስት በመተላለፍ የሚጣል ቅጣት**

፩/ የደንቡን ክፍል ስድስት ድንጋጌዎች ተላለፎ የተገኘ ማናቸውም ሰው በተላለፈው በእያንዳንዱ ድንጋጌ ልክ ብር ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ ብር) አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል።

፪/ ኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ በትክክል እንዳይሰራ ለማድረግ የነካካ፣ ያመቻቸ፣ ወይም በአሰራሩ ጣልቃ የገባ ማናቸውም ሰው በወንጀል ተጠያቂ ከመሆኑ በተጨማሪ ብር ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሺህ ብር) አስተዳደራዊ መቀጫ ይቀጣል።

**፷፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ የተሻረው ደንብ ይህ ደንብ የፀና ከመሆኑ በፊት ባሉ የሂሳብ ጊዜዎች ለተከናወኑ ግብይቶች ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰነው ቀን አንስቶ በ፲፪ ወራት ውስጥ በደንቡ ክፍል ስድስት በተወሰነው መሰረት መፈፀም አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተደነገገው መሠረት መፈፀም ያልቻለ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት ለታክሱ ባለሥልጣን ማመልከቻ ለማቅረብ ይችላል።

## PART TWELVE

## EXEMPT IMPORTS

**62. Import of Gold for National Bank of Ethiopia**

An import of good to be transferred to the National Bank of Ethiopia shall be an exempt import under Article 1(g) of Schedule 3 regardless of the level of purity of the gold or the form in which it is imported.

## PART THIRTEEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**63. Penalty for Breach of Part Six of the Regulation**

1/ A person who fails to comply with any of the provisions in Part six of the regulation shall be liable for a penalty equal to Birr 100,000 (one hundred thousand Birr) for each failure.

2/ A person who tampers, manipulates, or interferes with the proper functioning of an electronic fiscal device commits an offence and shall be punishable with a fine not exceeding Birr 200,000 (two hundred thousand Birr) or to rigorous imprisonment for a term not exceeding three years, or both a fine and imprisonment.

**64. Transitional Provision**

1/ The repealed Regulations shall continue to apply for accounting periods preceding the effective date of these Regulations.

2/ A VAT-registered person shall comply with Part six of the regulation within a period of 12 months from the date specified in a Directive issued by the Ministry of Revenue.

3/ A person who is unable to comply with Sub-Article (2) of this Article shall apply, in writing, to the Tax Authority for an extension of time to comply with Sub-Article (2) of this Article.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ ቢያንስ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የ፲፪ ወራት የጊዜ ገደብ ለመጠናቀቅ ፴ ቀናት ሲቀረው ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚፈቀደው የጊዜ ገደብ ማረዘሚያ ፈቃድ ከስድስት ወራት ሊበልጥ አይችልም።

**፷፭. የተሻሩ ሕጎች**

፩/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር ፸፱/፩ሺ፱፻፺፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፪/ ማናቸውም ደንብ ወይም መመሪያ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን እስከሆነ ድረስ በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፷፮. የሚጸናበት ቀን**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፲፯**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

4/ An application under Sub-Article (3) of this Article shall be made at least 30 days before expiry of the 12 month period specified in Sub-Article (2) of this Article.

5/ An extension of time to comply with Sub-Article (2) of this Article shall not exceed 6 months.

**65. Repealed Laws**

1/ The Value Added Tax Regulations No. 79/2002 are repealed by these Regulations.

2/ No other Regulation or Directive may, in so far as it is inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this Regulation.

**66. Effective Date**

These Regulations shall come into force as of the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of March, 2025**

**ABIY AHMED (DR)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## አባሪ አንድ

## ከውጭ ወደሀገር ውስጥ ሲገቡ እና ሀገር ውስጥ ግብይት ሲፈጸምባቸው ከታክሱ ነጻ የተደረጉ ተጨማሪ አቅርቦቶች

፩. የእንስሳት መድኃኒት፣

፪. የመድኃኒት መርጫ፣

፫. ለሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች እና በሐኪም ለሚታዘዙ መድኃኒቶች ማምረቻ የሚውሉ ግብአቶች፣

፬. የፀረ ወባ ክትባት፣ ኮንዶም እና ለሕክምና ተቋማት የሚቀርብ ኦክስጅን፣

፭. ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣ የኮንስላር ጽ/ቤቶች፣ የዲፕሎማቲክ አቋም ያላቸው አለም አቀፍ ድርጅቶች እና ዲፕሎማቶች በአገር ውስጥ የሚፈጽሟቸው ግዢዎች፣

፮. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የፌደራል እና የክልል ፖሊስ ተቋሞች፣ የህዝብ ደህንነት ተቋሞች የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ወደ አገር የሚያስገቧቸው እና በአገር ውስጥ የሚገዟቸው ለመከላከያ እና ለህዝብ ደህንነት የሚያገለግሉ ዕቃዎች እና መሣሪያዎች፣ ለእነዚሁ አገልግሎት የሚዉሉ ክፍሎች እና አክሰሰሪዎች፣

፯. እህል እና ጥራጥሬ፡-

ሀ) ጤፍ፣

ለ) ስንዴ፣

ሐ) ገብስ፣

መ) በቆሎ፣

ሠ) ማሽላ፣

ረ) ዘንጋዳ፣

ሰ) ዳጉሳ ፣

ሸ) አጃ፣

ቀ) ሩዝ፣

በ) አተር፣ ባቄላ፣ ምስር፣ አኩሪ አተር፣ ሽምብራ፣ ግብጦ፣ ጓያ እና የመሳሰሉት ጥራጥሬዎች፣ እና

ተ) የእነዚህ ዱቄት፡፡

፰. የበሰሉ ወይም የተዘጋጁ ምግቦች/መጠጦች፡-

ሀ) እንጀራ፣

ለ) ዳቦ፣ እና

ሐ) ወተት፡፡

፱. ማናቸውንም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን በመንግሥት ተቋማት ለሚሰጡ ፈቃዶች እና አገልግሎቶች የሚፈፀም ክፍያ፤

፲. ለግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት የሚውሉ እና በጉምሩክ ታሪፍ መጽሐፉ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ ከተፈቀዱ ዕቃዎች ውስጥ “የተመደቡ” ተብለው የተዘረዘሩት የግብርና ዕቃዎች፤

፲፩. ያልተዘጋጁ ሸንኩርት፣ ድንች እና አትክልቶች፤ እና

፲፪. ምግብ ለማበልጸግ የሚውሉ ቫይታሚኖች (ቫይታሚን ኤ፣ ቢ፩፣ ቢ፪፣ ቢ፫፣ ቢ፮፣ ቢ፱፣ ቢ፲፪፣ ዲ፣ ፖታሽየም አዮዴት እና ዚንክ ኦካሳይድ)፡፡

## Annex I

**Additional supplies exempt from value added tax when imported and supplied within the country**

1. Veterinary medicines;
2. Medicine sprinkler;
3. Inputs for the manufacturing of medical devices and prescription medicines,
4. Anti-malarial vaccines, condoms, and oxygen supplied to medical institutions;
5. Purchases made by diplomatic missions, consular offices, international organizations with diplomatic status, and diplomats;
6. The importation and domestic purchase of goods and equipment used for defence and public safety purposes, as well as their parts and accessories, by the Ministry of National Defence, Federal and State Police Institutions, and Public Security Institutions, subject to the directive issued by the Ministry of Finance;
7. Cereals and pulses:
   a) Teff;
   b) Wheat;
   c) Barley;
   d) Maize;
   e) Sorghum;
   f) Zengada (Ethiopian millet) ;
   g) Dagusa (Finger millet) ;,
   h) Oats;
   i) Rice;
   j) peas; beans, lentil, soyabean; chickpeas፣ lupin bean (gebeto), *Grass pea (lathyrus sativus)* and other similar grains; and
   k) Powder of these.
8. Cooked or prepared foods/drinks:
   a) Injera;
   b) Bread;and
   c) Milk.

9. Payments made to government body for business licenses and permits to conduct any activities;
10. Agricultural goods intended for agricultural mechanization, which are classified as eligible for duty and tax exemptions in the customs tariff book;
11. Unprepared onions, potatoes and vegetables; and
12. Vitamins used to fortify food (vitamins A, B1, B2, B3, B6, B9, B12, D, potassium iodate and zinc oxide).